# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

83ኛ ዓመት ቁጥር 032 ጥቅምት 2 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







ፎቶ፡ እዮብ ተፈራ

# “ግብር በመክፈል ለሕዝብና ለመንግሥት መታመን አርበኝነት ነው”

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

**ጌትነት ምህረቴ**

አዲስ አበባ፡- በሀቀኝነት ግብር በመክፈል ለሕዝብና ለመንግሥት መታመን አረበኝነት ነው ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) 5ኛው ዙር የታማኝ ግብር ከፋዮች የምስጋናና ዕውቅና መርሀ ግብር ትናንት በአንድነት ፓርክ ሲካሄድ እንደገለጹት፤ ሠርቶ፣ ለፍቶ፣ ዜጎችን አሠርቶ፣ የሚገባን አስቀርቶ ለሕዝብና ለመንግሥት የሚገባውን መስጠትም

“ግብር በመክፈል... ወደ ገጽ6 ዞሯል









# ዲጂታል ኢትዮጵያን የመፍጠሩ ጉዞ

**ተስፋ ፈሩ**

በኢትዮጵያ የዲጂታል ክፍያ አማራጮች በከፍተኛ ሁኔታ እየተስፋፉ መሆናቸውን የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታ እዮብ ተካልኝ (ዶ/ር) መግለጻቸው ይታወሳል፡፡ በዓመት እስከ አራት ትሪሊዮን የሚደርስ ብር በዲጂታል የክፍያ አማራጮች እየተዘዋወረ እንደሆነም ጠቁመዋል፡፡ ከ170 በላይ የመንግሥት ተቋማት የዲጂታል ግብይት ሥርዓት ውስጥ ገብተዋል። ለመሆኑ ይህ ጉዞ ምንን ያመለክታል?

በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የሚኒስትሩ ከፍተኛ አማካሪ የሆኑት ዐቢዮት ባዩ (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ የዲጂታል ኢትዮጵያ ስትራቴጂው ዋና ዓላማ በኢትዮጵያ አካታች የሆነ ዲጂታል ኢኮኖሚን ማልማት ነው፡፡

ዲጂታል ኢትዮጵያ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# “ዩኒቨርሲቲው የመምህራንን ክብር የሚመልሱ ተመራቂዎችን ማፍራት ይጠበቅበታል”

-ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ የትምህርት ሚኒስትር

**አመለወርቅ ከበደ**



አዲስ አበባ፡- የኮተቤ ትምህርት ዩኒቨርሲቲ የመምህራንን ክብር የሚመልሱ ተመራቂዎችን ማፍራት ይጠበቅበታል ሲሉ የትምህርት ሚኒስትር ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ ገለጹ፡፡

ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ እንደገለፁት፤ ዩኒቨርሲቲው በማኅበረሰቡ ዘንድ መምህራን ያጡትን ክብር የሚመልስ ተማሪ ማፍራት ይጠበቅበታል።

የትምህርት ዩኒቨርሲቲው በማስተማር ተግባሩ ጠንካራ የሞራል መሰረት ያላቸው፣ ሙያቸውን የሚያከበሩ መምህራንን ለሀገሪቱ ማብቃት ይጠበቅበታል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ዋነኛ

“ዩኒቨርሲቲው የመምህራንን... ወደ ገጽ6 ዞሯል



# “በሩብ ዓመቱ ኢትዮጵያ ስኬታማ የሁለትዮሽና የባለብዙ ወገን የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ አከናውናለች”

- አምባሳደር መለስ አለም
የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ

ገጽ 6






# የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ምርቶች የደኅንነት ማረጋገጫና ቁጥጥር አዋጅ ተዘጋጀ

**ዘላለም ግዛው**



አዲስ አበባ፡- የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሀገርን ብሄራዊ ደኅንነት ለማስጠበቅ፤ በዜጎች ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ጥቃቶችን አስቀድሞ ለመከላከል እና ለመቀነስ ያስችላል ያለውን አዋጅ ለዝርዝር ዕይታ ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ መራ፡፡

ምክር ቤቱ ትናንት በዋለው ሦስተኛ ዓመት የሥራ ዘመኑ አንደኛ መደበኛ ስብሰባው የቀረበለትን፤ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ምርቶች የደኅንነት ማረጋገጫና ቁጥጥር አዋጅ መርምሮ ነው ለዝርዝር እይታ የመራው፡፡

የአዋጁን ሃሳብ ለምክር ቤት አባላት ያቀረቡት የመንግሥት ዋና ተጠሪ ሚኒስትር አቶ ተስፋዬ በልጅጌ እንደገለጹት፤ ከኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ምርቶች ዕድገትና መራቀቅ ጋር ተያይዘው የሚመጡ አሉታዊ ተጽዕኖዎች በሀገራዊ የኢንፎርሜሽን ሀብቶች ደኅንነት መከላከል በማስፈለጉ አዋጁ እንዲወጣ ምክንያት ሆኗል፡፡

በዜጎች ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ጥቃቶችን አስቀድሞ መከላከልና መቀነስ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱም ለአዋጁ ድንጋጌ ምክንያት መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡

አዋጁ ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገባ የሚከለከሉ እና በገደብ የሚገቡ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ምርቶችን ለመለየት፣ የደኅንነት ማረጋገጫ ፈቃድ አሰጣጥን ሥርዓት ለመወሰንና በምርቶቹ ላይ ክትትል እና ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችል ግልጽ፣ ወጥ እና ፍትሐዊ አሠራር ይዘረጋል፡፡

በፍጥነት እያደገ የመጣው ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ሰዎች መረጃ የሚያገኙበት፣ የሚማሩበት፣ የሚሠሩበት፣ የሚጓጓዙበት የሚገበያዩበት፣ የሚዝናኑበትና የተለያዩ ማኅበራዊ አገልግሎት የሚያገኙበት ከፍተኛ ለውጦችን ማምጣቱም ተገልጿል።

እያደገ ከመጣው የኢንተርኔት መሠረተ ልማት አቅርቦት ጋር ተዳምሮ ሰዎች ከቴክኖሎጂ ጋር ያላቸው ቁርኝት በከፍተኛ ደረጃ በመጨመሩም የዜጎችን የሕይወት ጫና ማቅለሉም ተጠቁሟል፡፡ በመሆኑም የሀገርን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ምርቶች ደኅንነት ማረጋገጫ ቁጥጥር ሥርዓት የሀገሪቱን ደኅንነት በሚያስጠብቅ መልኩ በግልፅ፣ ወጥና ፍትሐዊ በሆነ እንዲሁም ሕግን መሰረት ባደረገ መልኩ ለመምራት አዋጅ ተዘጋጅቷል ብለዋል።

ቴክኖሎጂዎቹ በሀገር ደኅንነት ላይ ሊኖራቸው የሚችለውን አሉታዊ ተጽእኖ አስመልክቶ በቂ ግንዛቤ ለመፍጠር፣ መብትና ግዴታቸውን በግልጽ ለማስቀመጥ፣ ጥቅል የአሠራር ሥርዓቶችን ለመዘርጋት፣ ስጋት ለሚፈጥሩ ድርጊቶች ተገቢ እና ተመጣጣኝ እርምጃ ለመውሰድ እንዲሁም የሀገርን ብሄራዊ ደኅንነት ለማስጠበቅ እንደሚያስችልም ተናግረዋል፡፡

ምክር ቤቱ በትናንት ውሎው የተለያዩ የብድር ስምምነቶችን አጽድቋል፡፡ በኢትዮጵያ እና የዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮግራም ማስፈጸሚያ በተመሳሳይም ለሰው ሀብት ልማት ኦፕሬሽን ማስፈጸሚያ የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማድረግ የቀረበውን አዋጅ መርምሮ አጽድቋል፡፡

በኢትዮጵያና በጣሊያን መንግሥት መካከልም ለኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን የቡና እሴት ሰንሰለትን ማሻሻያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ፣ ለኢንዱስትሪ ዘርፍ የግብርና ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ ፓርክ ልማት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ እና ለውሃ እና ኢነርጂ ዘርፍ የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር የተደረጉ የብድር ስምምነቶችንም አጽድቋል፡፡

የምክር ቤት አባላቱ በውይይታቸው ለሰው ሀብት ልማት ኦፕሬሽን ማስፈጸሚያ የጸደቀው መሰረታዊ አገልግሎቶችን ጤናና ትምህርትን እንዲያማክል አሳስበዋል፡፡ በተለይም የመምህራን የብቃት እና ጥራት አሁን በተማሪዎች ውጤት ማነስ ላይ ለሚታየው ችግር ሚና ስላላቸው ብድሩ በባለሙያዎቹ ብቃት ጉዳይ ትኩረት ሊያደርግ እንደሚገባ አንስተዋል፡፡

ከተገኘው የ350 ሚሊዮን ዶላር ዕርዳታ እና የ50 ሚሊዮን ዶላር ብድር ውስጥ 135 ሚሊዮን ዶላሩ የአሠራር ሥርዓትን ማስተካከል ላይ በማተኮር የጤናና የመምህራን የአሠራር ብቃት ላይ እንደሚያተኩር ከገንዘብ ሚኒስቴር የተወከሉ ኃላፊ አቶ ኮከብ ምስራቅ ጠቁመዋል፡፡

የምክር ቤት አባላቱ ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የተገኘው ብድር በተገቢው መንገድ እንዲመራ፣ የተጨማሪ ኃይል ፍላጎትን ለመመለስና የኃይል መቆራረጥን ለማስቀረት ትኩረት እንዲደረግ አሳስበዋል፡፡

# በክልሉ ከ85 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት እንደሚመረት ይጠበቃል

**ፍሬሕይወት አወቀ**

አዲስ አበባ፡- በ2015/16 የምርት ዘመን በክልሉ በበልግና በመኸር ወቅቶች ከ85 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት እንደሚገኝ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል የግብርና ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊና የእርሻ ዘርፍ ኃላፊ አቶ አሸናፊ ክንፉ ገለጹ፡፡

ምክትል ቢሮ ኃላፊው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2015/16 የምርት ዘመን በበልግና በመኸር ወቅቶች ከአዝርዕትና ከሆርቲካልቸር ምርት በአጠቃላይ ከ85 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ይጠበቃል ብለዋል፡፡

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል በ2015/16 ዓ.ም የመኸር ወቅት አጠቃላይ 323 ሺህ 294 ሄክታር መሬት በአዝርዕት ሰብሎች ለማልማት አቅዶ ሲሠራ ቆይቷል ያሉት የቢሮ ኃላፊው፤ 322 ሺህ 911 ሄክታር መሬት በሰብል ዘር መሸፈን እንደተቻለና ከዚህም ሰባት ሚሊዮን ኩንታል ምርት እንደሚገኝ ነው የተናገሩት፡፡

በበልግ ወቅትም እንዲሁ በክልሉ ሰፊ ማሳ በዘር የተሸፈነ መሆኑን የገለጹት የቢሮ ኃላፊው፤ 325 ሺህ 556 ሄክታር መሬት በዘር መሸፈን እንደተቻለ ተናግረዋል፡፡ ይህም በመኸር ወቅት ከተዘራው ምርት ጋር ሲደመር በአጠቃላይ 650 ሺህ ሄክታር አካባቢ የሚደርስ ማሳ በሰብል ብቻ መሸፈን እንደቻለ አመላክተዋል፡፡

በበልግ ወቅት ከተመረተው ምርት 11 ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይገኛል ተብሎ የሚጠበቅ መሆኑን የገለጹት የቢሮ ኃላፊው፤ በመኸር ወቅት ከሚጠበቀው ሰባት ሚሊዮን ኩንታል ምርት ጋር በድምሩ ከ18 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የአዝርዕት ምርት ይገኛል ብለዋል፡፡

የሆልቲካልቸርና ቋሚ ሰብሎችን ጨምሮ በበልግና በመኸር ወቅቶች በሰብል የተሸፈነው መሬት ወደ ዘጠኝ መቶ ሺህ ሄክታር መሬት ይደርሳል ያሉት የቢሮ ኃላፊው፤ በዚህም በክልሉ አጠቃላይ በአዝርዕት ሰብሎችና በሆልቲካልቸር ምርቶች ጭምር በዓመት እስከ ዘጠኝ መቶ ሺህ ሄክታር መሬት የሚሸፈን እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ በመሆኑም ክልሉ በአዝርዕት ሰብሎችና በሆልቲካልቸር ምርቶች ከ85 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት በሁለቱ ወቅቶች መሰብሰብ እንደሚችል አመላክተዋል፡፡

በክልሉ በመኸር ወቅት በዋናነት 10 ሺህ ኩንታል ምርጥ ዘር ለማቅረብ አቅዶ የተመሰከረለት ዘርና ምርጥ ዘር በድምሩ 15 ሺህ 765 ኩንታል ምርት ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል ያሉት የቢሮ ኃላፊው፤ በተያያዘም 36 ሺህ 356 ሄክታር መሬት የሚሸፍን የአፈር ማዳበሪያ ጥቅም ላይ መዋሉንም ተናግረዋል፡፡

እንደ ኃላፊው ገለፃ፤ በክልል በማሳ ሽፋን ከዕቅድ በላይ መሄድ የሚችልበት ዕድል የነበረው ቢሆንም በወረሃ ነሐሴ ዝናብ የተቋረጠ በመሆኑ በተገቢው መንገድ ዘር መዝራት እንዳልተቻለ አስታውሰው፤ በዝናቡ መቋረጥ ምክንያት ከተዘሩት ሰብሎች ውስጥ ስምንት ሺህ ሄክታር ያህሉ መበላሸቱንና በሌላ ሰብል እንዲተካ መደረጉንም አመላክተዋል፡፡



# ከኮንስትራክሽን ግብዓቶች 80 በመቶ ያህሉን በሀገር ውስጥ ለማምረት እየተሠራ ነው

## -17ኛው ዓለም አቀፍ የኮንስትራክሽን ኤግዚቢሽን ተከፍቷል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- በሚቀጥሉት 10 ዓመታት 80 በመቶ የሚሆነውን መሠረታዊ የኮንስትራክሽን ግብዓት በሀገር ውስጥ ለማምረት በእቅድ ተይዞ እየተሠራ መሆኑን የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትር ዴኤታ ኢንጂነር ወንድሙ ሴታ 17ኛውን "ኢትዮ-ኮን 2023" ዓለም አቀፍ የኮንስትራክሽን ኤግዚቢሽንን ትናንት ሲከፍቱ እንዳሉት፤ ኢትዮጵያ ለኮንስትራክሽን ግብዓት የሚሆን በቂ ሀብት ቢኖራትም 65 በመቶ የሚሆነው የኮንስትራክሽን ግብዓት ከውጪ የሚመጣ ነው፡፡

በመሆኑም ችግሩን ከመሠረቱ ለመቅረፍ በሚቀጥሉት 10 ዓመታት 80 በመቶ የሚሆነውን መሠረታዊ የኮንስትራክሽን ግብዓት በሀገር ውስጥ ለማምረት በእቅድ ተይዞ እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

የኮንስትራክሽን ዘርፉ ሀገራችንን ከነበረችበት የድህነት ታሪክ አውጥተን በብልጽግና ማማ ላይ ለማኖር በምንሄድበት ሁሉም መንገዶቻችን ላይ የሚኖረው ሚና ከፍተኛ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ባለፉት 20 ዓመታት የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ በየዓመቱ በአማካይ 300 ቢሊዮን ብር የሚጠጋ ሀብት ለጥቅል ሀገራዊ ምርት አስተዋጽኦ ነበረው ብለዋል፡፡ አሁን ላይም ዘርፉ 480 ሚሊዮን ብር የሚጠጋ ሀብት ለጥቅል ሀገራዊ ምርት ያበረክታል፤ በሥራ እድል ፈጠራም ከግብርና ቀጥሎ ከፍተኛውን ድርሻ ይወስዳል ሲሉም ተናግረዋል፡፡

በመሆኑም ይህን ዘርፍ በአግባቡ መምራትና ከነበረበት ችግር ማውጣት ቀጣይ እንደ ሀገር የታለመውን ብልጽግና የማሳካት አንዱ ግብ መሆኑን ጠቅሰው፤ ለዚህ ትልም እውን መሆን መሰል ዓለም አቀፍ ኤግዚቢሽኖች ጥሩ አቅም ይፈጥራሉ፤ በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመፍታትም ያግዛል ብለዋል፡፡

ዘላቂ የኮንስትራክሽን ግብዓት ችግር ዋነኛው የዘርፉ ፈተና መሆኑን ገልጸው፤ ኢትዮጵያ ለኮንስትራክሽን ግብዓት የሚሆን በቂ ሀብት ቢኖራትም 65 በመቶ የሚሆነው የኮንስትራክሽን ግብዓት ከውጪ የሚመጣ ነው፡፡ ችግሩን ለመቅረፍ በሚቀጥሉት 10 ዓመታት 80 በመቶ የሚሆነውን መሠረታዊ የኮንስትራክሽን ግብዓቶች በሀገር ውስጥ ለማምረት ታቅዷል ብለዋል፡፡

ሌላኛው የዘርፉ ማነቆ የሀገር ውስጥ ሥራ ተቋራጮች፣ ባለሙያዎችና አማካሪዎች ተወዳዳሪነት ማነስ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ የዘርፉን ሁሉን አቀፍ ተወዳዳሪነት ለማሳደግ ሁሉንም ባለድርሻ አካላት በማስተባበር እየተሠራ እንደሆነም ተናግረዋል፡፡

በተጨማሪም የቴክኖሎጂ አጠቃቀም፣ የፋይናንስ ችግርን መቅረፍ፣ የሰለጠነ ሰው ኃይል ማቅረብና የሥራ ደኅንነትን በማረጋገጥ የዘርፉን ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ሥራ ተቋራጮች ማኅበር ፕሬዚዳንት ኢንጂነር ግርማ ሀብተማርያም በበኩላቸው፤ ያለፉት ጥቂት ዓመታት የሀገራችን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪና ተዋናዮቹ ዘርፈ ብዙ ተግዳሮቶች ሲጋፈጡ ቆይተዋል ብለዋል፡፡

የግንባታ ግብዓቶች የዋጋ ንረት፣ የግብይት ሥርዓቱ ፈታኝ መሆን፣ ሥራ ተቋራጮች ለሠሯቸው ሥራዎች ወቅቱን ጠብቆ ክፍያ አለመፈጸም እና በገንዘብ ፍሰታቸው ላይ እያስከተለ ያለው ጫና መፍጠሩ ካጋጠሙ ችግሮች መካከል መሆናቸውን ጠቅሰው፤ የግንባታ አገልግሎት ግዢ በፍትሐዊነት ባለመመራቱ ሥራዎች በጥቂት ሥራ ተቋራጮች የመያዝና ብዙኃኑን ከሥራ ውጪ የመሆን ችግሮች እንደነበሩም ጠቁመዋል፡፡

ዘርፉ ለሀገር ከሚያበረክተው አስተዋጽኦ አንጻር ያሉበት ችግሮች በወቅቱ መፍትሔ ሊያገኙ እንደሚገባ ገልጸው፤ ችግሮችን ለመቅረፍ ማኅበሩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅርበት እየሠራ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

በአዲስ አበባ ኤግዚቢሽን ማዕከል የተከፈተው 17ተኛው "ኢትዮ -ኮን 2023" ዓለም አቀፍ የኮንስትራክሽን ኤግዚቢሽን የኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ሥራ ተቋራጮች ማኅበር ያዘጋጀ ሲሆን፤ ከጥቅምት አንድ እስከ 4 ቀን 2016 ዓ.ም ለዕይታ ክፍት ሆኖ ይቆያል።

# የጀርመን መንግሥት በግጭት ለተጎዱ አካባቢዎች ከ10 ሚሊዮን ዩሮ በላይ የድጋፍ ስምምነት አደረገ

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- የጀርመን መንግሥት በሰሜኑ ግጭት ለተጎዱ አካባቢዎች የ10 ነጥብ አንድ ሚሊዮን ዩሮ ድጋፍ ለማድረግ ከዩኤንዲፒ ጋር በትናንትናው ዕለት ስምምነት ተፈራርመዋል፡፡

በስምምነቱ ወቅት ንግግር ያደረጉት በኢትዮጵያ የጀርመን አምባሳደር ስቴፋን አውየር፤ ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ዋነኛ አጋሮቻችን አንዷ ነች ብለው የዛሬው ስምምነት የተደረገው ጀርመን ኢትዮጵያ ግጭት ለማስቆም የምታደርገውን ጥረት ስለምትደግፍ ነው፡፡ አሁን ለመጣው ሰላምም መነጋገርና መወያየት ግጭትን ለመፍታት ብቸኛ መንገድ መሆኑን ማሳያ ነው ብለዋል፡፡

እንደ አምባሳደሩ ገለጻ፤ በአፍሪካ ቀንድ ሰላምና መረጋጋት ሊኖር የሚችለው ሰላም የሆነች እና አንድ የሆነች ኢትዮጵያ ስትኖር ብቻ ነው። ይህን ሰላም ለመደገፍም ጀርመን እና የዩኤንዲፒ አጋርነት ትልቅ አስተዋጽኦ አለው፡፡ ጀርመን ይህን ስምምነት በመፈረሟ ለዩኤንዲፒ ከ10 ሚሊዮን ዩሮ በላይ ታወጣለች፡፡

በቀጣይ ሁለት ዓመታትም በኢትዮጵያ የተጀመረውን የመልሶ ማቋቋም እና መልሶ ግንባታ ሥራ አጠናክሮ ለመቀጠል በትኩረት እንደሚሠራ የገለጹት አምባሳደሩ፤ በሰሜኑ ኢትዮጵያ የሰፈነውን ሰላም ለማጽናትም የድርሻቸውን እንደሚወጡ ተናግረዋል፡፡

በኢትዮጵያ የዩኤንዲፒ ተወካይ ሚስተር ቱርሃን ሳሌህ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት ወደ ዘላቂ ሰላምና ልማት በመሸጋገር ላይ ያለች ሀገር ናት፡፡ እስካሁንም በተሠራ ሥራ በአፋር፣ በአማራና በትግራይ በሚገኙ 13 በግጭት ለተጎዱ ወረዳዎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለአንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሕዝቦች ተደራሽ የሆነ ድጋፍ ማድረግ ተችሏል ብለዋል፡፡

በጀርመን መንግሥት አጋዥነትም በፈረንጆቹ 2024 ይህን ቁጥር እጥፍ ለማድረግ ይሠራል ሲሉም አክለዋል፡፡

ሌላ ሀገራት የጀርመን መንግሥት ያደረገውን በጎ ተግባር እንደ ምሳሌ ሊወስዱ ይገባል ያሉት ተወካዩ፤ ዩኤንዲፒ በበኩሉ ስምምነቱ የተሳካ እንዲሆን ያለውን አቅም ተጠቅሞ ይሠራል ሲሉ ገልጸዋል፡፡ በዚህም ከፌዴራል ከክልልና ከልማት አጋሮች ጋር በመሆን ድጋፉ ለታለመለት ዓላማ እንዲውል ይሠራል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በግጭቱ ለተሰቃዩ ወገኖች፣ ሰላም እውነተኛ እፎይታ እና ጠቃሚ ዕድሎችን እንደሚያመጣ ማሳየት ያስፈልጋል ያሉት ተወካዩ ፤ የጀርመን መንግሥት ላደረገው የድጋፍ ስምምነት ምስጋናቸውን አቅርበዋል፡፡

# በ2022፣ 20 ሚሊዮን የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዷል

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ የሥራ አጥ ቁጥርን ለመቀነስ እስከ 2022 ዓ.ም 20 ሚሊዮን የሥራ እድል ለመፍጠር አቅዳ እየሰራች መሆኗን የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ንጉሡ ጥላሁን አስታወቁ:: በሥራ ፈጠራ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ላይ ትኩረት ያደረገው “እንቆጳ” የተሰኘው ጉባዔ መካሄድ ጀምሯል::

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የሥራ፣ ሥራ ሥምሪትና ገበያ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ንጉሡ ጥላሁን የ“እንቆጳ” ጉባዔን ትናንት በከፈቱበት ወቅት፤ በአፍሪካ በሕዝብ ብዛት በሁለተኛ ደረጃ ላይ የምትገኘው ኢትዮጵያ በከፍተኛ ደረጃ እየተስተዋለ ያለውን የሥራ አጥነት ሁኔታ ለመለወጥ እየጣረች ትገኛለች ብለዋል:: ከጊዜ ወደ ጊዜ ፈተና እየሆነ የመጣውን የሥራ አጥነት ቁጥር ለመቀነስ በሀገር ደረጃ በ2022 ዓ.ም 20 ሚሊዮን የሥራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ እየተሠራ እንዳለም አመላክተዋል::

በብሄራዊ ሪፎርም ለሥራ እድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዞች ልማት ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ ይገኛል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ማሻሻያው ኢንተርፕራይዞቹ ምቹ የሥራ እድል እንዲፈጥሩና የንግድ ሥነ-ምህዳሩን ለማስፋት ያለመ እንደሆነ ጠቁመዋል:: ይህም ኢኮኖሚያዊ ሀብትን ለመፍጥር የሚያስችል እንደሆነ ገልጸዋል::

መንግሥት፣ የግሉ ሴክተርና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የተቀናጀ ጥረት በማድረግ በተለይ የዲጂታል



**አቶ ንጉሡ ጥላሁን**

ሥራ ፈጠራ አቅምን መጠቀም እንዳለባቸው ተናግረው፤ ይህ ካልሆነ ግን ሪፎርሙ የሥራ እድል ፈጠራንና የኢንተርፕራይዞች ልማትን ግብ በዘላቂነት ሊያሳካው እንደማይችል ተናግረዋል:: በዚህ ረገድ ሚኒስቴሩ ለሀገሪቷ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ጠንካራ የሥራ ዕድል ፈጠራ ሥነ-ምህዳር ለመገንባት በቁርጠኝነት እየሠራ ነው ብለዋል:: በዚህም በሀገር አቀፍ ደረጃ በ2022 ዓ.ም 20 ሚሊዮን የሥራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ እየተሠራ እንዳለ አመላክተዋል::

በብሔራዊ ዲጂታይላዜሽን ጥረቶች በመታገዝ የተጀመሩ ፈጠራዎች ዘላቂ ኢኮኖሚያዊ ብልጽግናን ያመጣሉ ተብሎ እንደሚጠበቅም ሚኒስትር ዴኤታው አንስተዋል:: የዲጂታል ኢኮኖሚና የዲጂታል ሥራ አዲስ ክስተት እንደመሆኑ የግንዛቤ ፈጠራ፣ የሚዲያ ዘመቻና የፖሊሲ ቅስቀሳ እንደሚያስፈልገው ነው የጠቆሙት::

እ.ኤ.አ. በ2021 የኢትዮጵያን የሥራ ፈጠራ እንቅስቃሴ ለማስተዋወቅ እንቆጳ የተሰኘ ሀገራዊ ንቅናቄ እንደተጀመረ ያነሱት አቶ ንጉሡ፤ ቴክኖሎጂን ያፈለቁ ጀማሪ ሥራ ፈጣሪዎች ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ተዋውቀው ድጋፍ የሚያገኙበት መድረክ እንደሆነም ተናግረዋል::

ጉባዔው የኢንዱስትሪ ኃላፊዎችን፣ የድርጅት ሥራ አስፈጻሚዎችን፣ መሐንዲሶችን፣ ጀማሪ ሥራ ፈጣሪዎችን፣ ፖሊሲ አውጪዎችንና ምሁራንን ያሳተፈ መሆኑን ገልጸዋል::

ትናንት የተጀመረው የእንቆጳ ጉባኤ በአፍሪካ ሀገራት መካከል ያለውን ትብብር ለማሳደግና በሥራ ፈጠራ ኢትዮጵያ እንደ ትልቅ የኢንዱስትሪ ክስተት ያላትን ጸጋና አቅም ለማጋራት ያስችላታል ብለዋል:: ኢትዮጵያን በማስተዋወቅ ከፍተኛ የሥራ እድል ለመፍጠር ምቹ አጋጣሚ መሆኑንም ጠቅሰዋል::

በጉባዔው ከ26 ሀገራት የተውጣጡ አካላት የተሳተፉ ሲሆን፤ በዛሬው እለት እንደሚጠናቀቅ ለማወቅ ተችሏል::

“እንቆጳ” በግእዙ ቋንቋ “የወርቅ ጥሬ ሀብት” የሚል ትርጓሜ ያለው ሲሆን፤ የሥራ ፈጠራ ዘርፉ ያሉበትን ተግዳሮቶች በመቅረፍ በሚገባ ማንቀሳቀስ ከተቻለ ሊያብረቀርቅ የሚችል መልካም እድል ያለው መሆኑን የሚያሳይ ነው::



መሠረታዊ ወታደር አቤል በዋለ፤

ፎቶ፡ ገባቦ ገብሬ



ምክትል 10 አለቃ ጤናው አሰማው



ሻምበል አዲሱ ጋሻው

# “በኮሌጁ ቆይታችን ባገኘነው ዕውቀት ሀገራችንን ይበልጥ ለማገልገል ዕድል አግኝተናል”

## - የውጊያ ምህንድስና ኮሌጅ ምሩቃን

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- በኮሌጁ ቆይታችን ባገኘነው ዕውቀት ሀገራችንን በብቃት ለማገልገል ዕድሉን አግኝተናል ሲሉ በመከላከያ ትምህርትና ስልጠና ዋና መምሪያ የውጊያ ምህንድስና ኮሌጅ ምሩቃን ገለጹ፡፡

ከኮሌጁ በመሠረታዊ የውጊያ ምህንድስና በማዕረግ የተመረቀው ወታደር አቤል በዋለ፤ በኮሌጁ በነበረው ቆይታ ከአሠልጣኞቹ ማግኘት ያለብኝን ተገቢውን ዕውቀት አግኝቻለሁ፤ ባገኘሁት ክህሎት ሀገሬን በብቃት ለማገልገል ዕድሉ ተፈጥሮልኛል ሲል ለኢፕድ ተናግሯል፡፡

ተዋጊ መሐንዲሱ ለሠራዊቱ አመቺ ሁኔታዎችን መፍጠር ቀዳሚ ተግባሩ ነው፤ እግረኛው ጦር ግዳጁን የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ እንዲወጣ የተዋጊ መሐንዲስ ሚና ትልቅ ነው። በዚህ ረገድ ዘመኑ የሚጠይቀውን ዕውቀት አግኝቻለሁ ብሏል።

ከአዲግራት ዩኒቨርሲቲ በሂሳብ መዝገብ አያያዝና በፋይናንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ከተመረቀ በኋላ የውትድርናውን ዓለም እንደተቀላቀለ የገለጸው ወታደር አቤል፤ በኮሌጁ ቆይታው ለሀገር የሚጠቅም ሥራ ማከናወን የሚያስችለውን ክህሎት ማግኘቱን ተናግሯል።

የሀገራቸውን ዳር ድንበር ለማስጠበቅና በሙያዊ ስነምግባር ለማገልገል ዝግጁ መሆናቸውን ለኢፕድ የገለጹት ከማዕከላዊ ዕዝ 33ኛ ክፍለ ጦር የመጡት ሰልጣኝ ምክትል 10 አለቃ ጤናው አሰማው ናቸው፡፡

እንደ ምክትል አስር አለቃ ጤናው ገለጻ፤ በውትድርናው ዓለም ተዋጊ መሐንዲስ ለወገን ጦር ደራሽ እና የጀርባ አጥንት ነው፡፡

ከዚህ ቀደም የማያውቃቸውን የዘርፉን ክህሎቶች ማግኘቱን የገለጸው ምክትል 10 አለቃ ጤናው፤ በጦርነት ወቅት መንገድና ድልድይ ዋናው መሰናክል ሊሆን ይችላል፤ በኮሌጁ ቆይታው መሰናክሎቹን በማለፍ የወገንን ጦር እንዴት መደገፍ እንደሚቻል ዘመኑ የሚጠይቀውን ሙያ ቀስሜያለሁ ሲል ገልጿል።

አክሎም ወታደር ለሕዝብና ለሀገር ቀድሞ የሚከፍል ዋጋ በመሆኑ በገባሁት ቃልኪዳን መሰረት ሕዝብና ሀገርን በሙያው ለማገልገል ዝግጁ መሆኑን አስታውቋል።

በውጊያ ምህንድስና ኮሌጅ አሰልጣኝ የሆኑት ሻምበል አዲሱ ጋሻው በበኩላቸው፤ ሰልጣኞቹ በኮሌጁ በነበራቸው ቆይታቸው በክፍል ውስጥ ትምህርትና በመስክ ልምምድ በቂ ክህሎት እንዲጨብጡ መደረጉን አስረድተዋል።

እንደ ሻምበል አዲሱ ገለጻ፤ በውጊያ ምህንድስና አመራርነትና መሰረታዊ የውጊያ ምህንድስና ዘመኑ የሚጠይቅ መሰረታዊ የውጊያ ምህንድስና ሰልጣኞች 70 በመቶውን በመስክ ልምምድ ያጠናቀቁ ሲሆን፤ የተቀረውን 30 በመቶ በክፍል ውስጥ ትምህርት ሸፍነዋል።

በአንጻሩ ለአመራር ሰልጣኞች 60 በመቶ የመስክ ልምምድና 40 በመቶውን የጽንሰ ሃሳብ ትምህርት እንዲቀስሙ መደረጉን ጠቁመዋል።

ሰልጣኞቹ ያገኙትን እውቀት ለመፈተሽ ሲባል በወሰዷቸው ዋና ዋና ኮርሶች በመንገድና ድልድይ ሥራ፣ የውሃ ማጣራት እና በመሳሰሉት ዘርፎች ጊዜው የሚጠይቀውን ብቃት ይዘው እንዲወጡ ተደርጓል።

ተመራቂዎች ባገኙት ዕውቀት በሀገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ሀገራት ሰላም ማስከበር ግዳጆች ተሰልፈው ውጤታማ ሥራ እንዲያከናውን የሚያስችል ግብዓት ማግኘታቸውን አስታውቀዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የታመነን ማመስገን የላቀ ኃላፊነት የሚሰማው ታማኝ ዜጋን ይፈጥራል!

የአንድ ሰው ታማኝ መሆን ለራስ ብቻ ሳይሆን፤ ለቤተሰብ፣ ለማሕበረሰብ ብሎም ለሀገር ያለውን ከፍ ያለ ፍቅር፣ ክብር እና ስለነዚህ አካላት ከፍ ያለ ኃላፊነት የመሸከም ልዕልናን መግለጫ ነው:: ምክንያቱም ታማኝነት ለራስ ከፍ ያለ ክብርና የስብዕና መግለጫ ከመሆኑም ባሻገር፤ ከፍ ያለ ኃላፊነት የመሸከምና የመወጣትም አቅምን ብቻ ሳይሆን፤ ለሕግ፣ ለሞራል እና ለየማኅበረሰብ እሴቶች ተገዢነትን ማሳያ ነው::

አንድ ሰው ሲታመን ለራሱም ለቤተሰቡም ክብር ነው፤ በቤተሰቡ ውስጥ መታመንን የተለማመደ ትውልድ ደግሞ ለማሕበረሰቡም ለሀገር የታመነ ይሆናል:: ለዚህ ነው ቤተሰብ ላይ የሚሰራ ሥራ ሀገርን መገንባትም፣ ማፍረስም የሚችል ምግባር የተላበሰ ትውልድን እንደሚፈጥር በብዙ መልኩ ሲገለጽ የሚሰማው::

የመታመን መገለጫዎች ደግሞ ዘርፈ ብዙ ናቸው:: ከእነዚህ መካከል ለዛሬው ለሀገርና ሕዝብ መታመን ውስጥ የሚገለጸውን የታማኝ ግብር ከፋይነት ይገኝበታል:: በተለይ ግብር ለአንድ ሀገር እና ለሀገረ መንግስት ሕልውና ከሚኖረው አይተኬ አበርክቶ አኳያ፤ በየትኛውም ሀገር የግብር ጉዳይ ትልቅ ትኩረት የሚሰጠው ነው::

ምክንያቱም አንድ ሀገር ማሕበራዊም፣ ኢኮኖሚያዊም፣ ፖለቲካዊም ሆነ የደኅንነትና ሉዓላዊነት ጉዳይዋ መሠረት ሊኖረው የሚችለው፤ እነዚህን ጉዳዮች ማራመጃ የሚሆን የገንዘብ አቅም፣ የፋይናንስም ምንጭ ሲኖር ነው:: የሀገራት ተሞክሮ እንደሚያሳየው ደግሞ፣ የአንድ ሀገር መንግስት ትልቁ የሀብት ምንጭ ግብር ነው::

በኢትዮጵያም ይሄው የግብር ጉዳይ እንደየወቅቱ የአሰባሰብ ሂደቱ ይለያይ እንጂ ለሺህ ዓመታት የነበረ፤ አሁንም ከዘመኑ ጋር ራሱን እያወዳጀ የቀጠለ ተግባር ነው:: ይሄ በመሆኑም ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ሕልውናዋ ተጠብቆ፤ መንግስትም እንደ መንግስት ሀገርን የማስተዳደር፤ የሕዝቦችን ጥያቄ የመመለስ አቅም ፈጥሮ ዘልቋል::

ይሁን እንጂ የግብር አሰባሰቡ ሂደት ሁሉም ነገር አልጋ በአልጋ ሆኖ የሚከወን ነው ማለት አይደለም:: ይሄ ደግሞ አንድም ከግብር ሰብሳቢው አካል፤ በሌላም በኩል ከግብር ከፋዩ ማሕበረሰብ ባሕሪ እና ፍላጎት ጋር የሚያያዝ ነው:: ይሄ የባህሪና ፍላጎት ጉዳይ ደግሞ ታምኖ ግብር የመሰብሰብና ያለመሰብሰብ፤ ታምኖ ግብር የመክፈልና ያለመክፈል ተቃርኖዎችን ይፈጥራል::

ለሀገርና ሕዝብ ታምኖ ግብር መሰብሰብና መክፈል እንዳለ ሁሉ፤ በአንጻሩ ከሀገርና ሕዝብ ሸሽጎ ለራስ ጥቅምና ፍላጎት በማድላት የሚገለጥ ብልሹ ባህሪ ምክንያት ግብርን በመሰወርና ለዚህ ተባባሪ በመሆን ውስጥ በሚታይ አለመታመን በእጅጉ ሀገርንም መንግስትንም የሚፈትኑ ጉዳዮች ናቸው::

እነዚህ በመታመንና አለመታመን ውስጥ ያሉ ሁለት ተቃርኖዎች ደግሞ፤ የዜጎችን ለሀገራቸው ያላቸውን ፍቅር የሚገልጹበት፤ ካልሆነም ግላዊ ፍላጎታቸውን ተከትለው የሚነጉዱበት ነው:: ከዚህም ባለፈ አንዱ ታምኖ የከፈለውን ክብር ሌላኛው ባልተገባ መንገድ መልሶ የሚወስደው፤ ሀገርና ሕዝብ የሚፈልጉትን እንዳያገኙም፣ እንዳይጠቀሙም የሚያደርግ አሰራር ነው::

ይሄን መነሻ በማድረግም፣ ግብር ሰዋሪዎችንና በመሰል ተግባር የሚገለጹትን የማረምና ወደ መስመር የማስገባት ርምጃዎች ለመውሰድ ተሞክሯል:: በዚህም የተወሰነ ለውጥም ማምጣት ተችሏል:: ይሁን እንጂ ታምነው ግብር የሚከፍሉ እና በሀገር ሁለንተናዊ ዕድገት ውስጥ የሚጠበቅባቸውን የሚወጡ ግብር ከፋዮች የሚበረታቱበት ሥርዓት አልነበረም::

ይሄም መልካም መሥራት የሚያስመሰግንና የሚያሸልም ስላይደለ፤ እንዲህ አይነት ታማኞችን ለማፍራት የሚደረገው ጥረት ላይ የራሱን ጫና መፍጠሩ አልቀረም:: ይሁን እንጂ ከለውጡ ማግስት ይሄንን ስሜት የሚቀይር አዲስ አሰራር እውን ሆነ:: ግብር ሰዋሪዎችን የማረም ብቻ ሳይሆን፤ በታማኝነት ግብራቸውን የሚከፍሉ አካላትን በአደባባይ ማመስገንና መሸለም ተጀመረ::

በ2012 ዓ/ም ላይ አንድ ብሎ የጀመረው ይሄ የእውቅናና ሽልማት መርሃ ግብር፣ ዘንድሮ ለአምስተኛ ጊዜ ተካሂዷል:: በመጀመሪያው ዙር .. ታማኝ ግብር ከፋዮችን የማመስገንና የመሸለም ተግባሩ ያሳደረው መልካም ሂደት፤ በሁለተኛው ዙር 200፣ በሦስተኛው ዙር 300፣ በአራተኛው ዙር 400 እንዲሁም በአምስተኛው ዙር 500 ታማኝ ግብር ከፋዮች እውቅናና ሽልማት አግኝተዋል:: በዚህ መልኩ ታማኝ ግብር ከፋዮችን የማመስገንና የመሸለም ሂደቶች ደግሞ ታማኝ ብቻ ሳይሆን የማይታመኑትን የሚያጋልጡ ዜጎች እንዲፈጠሩ ዕድል የሰጠ ሆኗል::

ለምሳሌ፣ በአራተኛው ዙር የዕውቅና እና ሽልማት መርሃግብር 400 ታማኝ ግብር ከፋዮች የተሸለሙ ሲሆን፤ ከእነዚህ መካከል 40ዎቹ የፕላቲኒየም፣ 120ዎቹ የወርቅ እና 240ዎቹ የብር ደረጃ ተሸላሚዎች ናቸው:: 14 ግብር ከፋዮች ደግሞ ለሦስት ተከታታይ ጊዜ እና ከዛ በላይ በመሸለም በልዩ ተሸላሚነት፤ አንድ ግብር ከፋይ ደግሞ ሙስናና ብልሹ አሰራርን በማጋለጥ ተሸላሚ ሆነዋል::

በአምስተኛው ዙር የታማኝ ግብር ከፋዮች የእውቅናና ሽልማት መርሀግብርም 50 በፕላቲኒየም፣ 150 በወርቅ፣ 300 በብር ደረጃ እንዲሁም፤ 14 ልዩ ተሸላሚዎች ምስጋናና እውቅና ተበርክቶላቸዋል:: ይሄን መሰሉ ታማኞችን የማመስገን ተግባር ደግሞ የታመኑትን የበለጠ እንዲታመኑ፣ በመታመናቸውም ክብርና ኩራት እንዲሰማቸው ከማድረጉም በላይ፤ ሀሰተኛ ግብር ከፋዮች ከእኩይ መንገዳቸው እንዲመለሱና የተሻለ ስብዕናን ተላብሰው ወደ ታማኝ ግብር ከፋይነት መስመር እንዲገቡ የሚያደርግ ነው!


## አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## የሁሉ ነገር መሰረት የሆነውን ትምህርት ከስብራት ለመታደግ

ፍሬሕይወት አወቀ

የማንኛውም ችግር መፍቻ ዘዴና ብልሃቱ ትምህርት ለመሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም:: በዓለም ላይ ለሚታዩ ለውጦች ሁሉ ጉልህ ሚና የመጫወት አቅሙ ትልቅ ነው:: ለአንድ አገር ዕድገትና ለውጥ ሁለንተናዊ የሆነ መፍትሔዎችን ያነገበ በመሆኑ ለተጠቀመበት የችግሮች ሁሉ ፍቱን መድሃኒት ከመሆን ባለፈ የአገር ካስመን የሚያጸና ነው:: ለዚህም ነው ትምህርትን በአግባቡ የተጠቀሙ እና ውጤታማ የትምህርት ሥርዓትን የተከተሉ የዓለም አገራት በተለያዩ ዘርፎች ቀዳሚ ሆነው የምንመለከተው::

በተለይም እንደ ኢትዮጵያ በማደግ ላይ ያሉ አገራት ከድህነት ለመውጣትና እንደ ሀገር ለማጽናት ብቸኛው መንገዳቸው ትምህርት ስለመሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም:: «ነገርን ከስሩ ውሃን ከጥሩ» እንዲሉ የሁሉ ነገራችን መሰረት ከስር መሰረቱ የጸና ይሆን ዘንድ እንደ አገር ትምህርትን ጠበቅ አድርጎ መያዝና ውጤታማ የትምህርት ስርዓትን መከተል አገርን ወደፊት ለማሻገር ይበጃል::

በተቃራኒው ደግሞ አገርን የኋሊት ለመጎተትና ለማጥፋት ዘመናዊ መሳሪያን ከመጠቀም ይልቅ የትምህርትን ዋጋ መቀነስ፣ ትምህርትን ማሽመድመድና ስብራት እንዲገጥመው ማድረግ በራሱ ብቻ በቂ እንደሆነ ይታመናል:: በዚህ ሂደት ትልቅ ዋጋ የከፈሉ ሀገራትም ጥቂት የሚባሉ አይደሉም። ከአብዛኞቹ ኋላቀር ደሀ ሀገሮች አሁነኛ ሀገራዊ እውነታ በስተጀርባ ጎልቶ የሚታየውም ይህው ነው።

አንድ አገር ትምህርትን በተገቢው መንገድ መጠቀም፤ ውጤታማ የትምህርት ስርዓትን መከተል ካልቻለ በትምህርት የሚገኙ ትሩፋቶችን ለማግኘት አይችልም:: ይህ ማለት ደግሞ ለመጪው ትውልድ የምናሻግረው አገርና ሕዝብ አይኖረንም ማለት ነው:: ለዚህም ነው ትምህርት ላይ በብዙ መሥራት የግድ የሚሆነው::

እርግጥ ነው እኛ ኢትዮጵያውያን ባለፉት ስድስት አስርቶች እንደ አገር በርካታ ስብራቶች አጋጥመውናል:: አሁንም እየፈተኑን ያሉ ለቁጥር የበዙ ስብራቶች ያሉብን ህዝቦች ነን፤ ከስብራቶቻችን ሁሉ የከፋው ግን በትምህርት ዘርፍ የገጠመን ለመሆኑ አያጠያይቅም:: ለዚህም ደግሞ ከሰሞኑ ይፋ የተደረገው ብሔራዊ የ12ኛ ክፍል ውጤት አንድ ማሳያ ነው:: የውጤቱ አስደንጋጭነት የትምህርት ዘርፉን ከሚመራው ትምህርት ሚኒስቴር ባለፈ መላውን ሕዝብ ያነጋገረና ያስደነገጠ ጉዳይ ነው::

የትምህርት ሚኒስቴሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ የ2015 ትምህርት ዘመን የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ውጤትን ይፋ ባደረጉበት ወቅት በጉዳዩ ላይ በሰጡት መግለጫ፤ በትምህርት ዘመኑ ፈተናውን ከወሰዱት 845 ሺ በላይ ተማሪዎች ውስጥ 50 በመቶና ከዛ በላይ ያመጡት 27 ሺ 267 ተማሪዎች ብቻ መሆናቸውን ገልጸዋል።

ይህም ከአጠቃላይ ተማሪዎች ሶስት ነጥብ ሁለት በመቶ የሚሸፍን ነው፤ ተማሪዎቻቸውን ካስፈተኑ ሶስት ሺ 106 ትምህርት ቤቶች መካከልም አንድ ሺ 328 ትምህርት ቤቶች አንድም ተማሪ ማሳለፍ እንዳልቻሉ ተናግረዋል:: ውጤቱ እንደ አገር በዘርፉ ውድቀት ላይ መሆናችንን የሚያሳይ ስለመሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም።

ተማሪዎቹ ከታች ጀምረው የመጡበት መንገድ የተጣመመና የተወላገደ ለመሆኑ ይኸው ውጤት ይናገራል:: ለጊዜው ለውድቀቱ ተጠያቂው ማነው የሚለውን ወደ ጎን በመተው እንደ አገር የደረሰብንን ስብራት ለመጠገን በሚያስችለን ጉዳዮች ዙሪያ እያንዳንዳችን ርብርብ ማድረግ ይጠበቅብናል::

በርግጥ በአገሪቱ የመጣውን ለውጥ ተከትሎ ለቁጥር የበዙ ኢኮኖሚያዊ፣ ማሕበራዊና ፖለቲካዊ ስብራቶቻችንን ለመጠገን አገር ወገቧን ታጥቃ ያለ ስስት ብዙ ርቀት ተጉዛለች:: በዚህም ውጤት የታየባቸው ዘርፎች ቀላል ግምት የሚሰጣቸው አይደሉም::

የሁሉም ነገር መሰረት በሆነው በትምህርት ዙሪያም አገር እንደ አገር ብዙ ሥራዎች ሰርታለች:: በዘርፉ ያጋጠመውን ስብራት ለመጠገን በትምህርት ፍኖተ ካርታ ኮንፈረንስና አገራዊ ጥናት በማካሄድ አገርን ለመጪው ትውልድ ለማቀበል ብዙ ደፋ ቀና ብላለች::ይህም ሆኖ

**ትናንትናችን ውስጥ የቱንም ያህል ችግሮች ቢኖሩ ዛሬም ያልተሻገርናቸው እጥረቶች ስለመኖራቸው መካድ አይቻልም**

ግን ውጤት አስደንጋጭ ሆኗል:: እርግጥ ነው ዛሬ ያስደነገጠን ውጤት የዛሬ አምስትና ስድስት ዓመታት ሥራ አይደለም ከዛም በላይ ተከማችቶ የቆየ ችግር ነው::

እሱ ሳይማር ልጆቹን የሚያስተምር ወላጅ ባለበት በእኛ አገር ደግሞ ውጤቱ ከማስደንገጥ በላይ ይሆናል:: ወላጆች የነገዋን ኢትዮጵያ በማሰብ ብዙ ዋጋ ሲከፍሉ ኖረዋል:: ችግሮቻቸውን ሁሉ ዋጥ ስልቅጥ አድርገው ባለ በሌለ አቅማቸው ምሳ ቋጥረውና የትምህርት ቁሳቁስ አሟልተው አገርን ከውድቀት ለመታደግ ተማር ልጄ በማለት ከዕውቀት ገበታ ሲልኩና ሲቀበሉ ለዓመታት ደክመዋል::

ተማሪዎችም እንዲሁ ካቅማቸው በላይ የሆነ ቦርሳ ተሸክመው ከትምህርት ቤት ተመላልሰው ከክፍል ክፍል ሲዘዋወሩ ኖረዋል:: እዚህ ጋር ቆም ብሎ ማሰብና ለመፍትሔው መትጋት እንደ አገር ከሁሉም የሚጠበቅ ነው። በተለይም ከምሁራኑና ከፖለቲካ ኢሊቱ ብዙ ሥራ ይጠበቃል::

ምንም እንኳን ለዛሬው ስብራታችን ትናንትናችን ተወቃሽ ቢሆንም፤ የትናንቱ ችግራችን እስከመቼ ነው ለዛሬው ውድቀታችን ምክንያት ሆኖ የሚቀጥለው የሚለው ግን መልስ ሊሰጠው የሚገባው የብዙዎቻችን ጥያቄ ነው:: ትናንትናችን ውስጥ የቱንም ያህል ችግሮች ቢኖሩ ዛሬም ያልተሻገርናቸው እጥረቶች ስለመኖራቸው መካድ አይቻልም::

ለአብነትም ከዚህ ቀደም አንድ ለአምስት የነበረው የተማሪዎች መጽሐፍ ካለፉት ሁለት ዓመታት ወዲህ ከተማሪዎች ቦርሳ ውስጥ አልታየም:: ለተማሪዎች ዕውቀትን ማቀበል ያለበት የተማሪ ኃይል እንደመሆኑ የመምህራኑ አቅምም እንዲሁ ሊፈተሽ የሚገባው ጉዳይ ነው:: እነዚህና መሰል ችግሮች ከትናንትናችን ጋር ተደምረው አስደንጋጭ የሆነውን የ12ኛ ክፍል የተማሪዎች ውጤት አስታቅፈውናል::

ውጤታማ ባልሆነ የትምህርት ስርዓት ውስጥ ያለፈ ተማሪ ነገ ከነገ ወዲያ መምህር፣ ሀኪም፣ መሀንዲስ፣ ኢኮኖሚስትና ሌላም ሌላም መሆን አይችልም:: ምንም መሆን ቢችል እንኳ ተሳስቶ የሚያሳስተን እና እንደ አገር አጥፍቶ የሚያጠፋን መሆኑ አይቀሬ ነው::

ትምህርት የሁሉ ነገር መሰረት እንደመሆኑ ትምህርት ላይ የተበላሸ ነገር ሁሉ ጥፋቱ የበዛ ነው፤ አገር እንደ አገር እንዳትቀጥል ማድረግ የሚያስችል አቅም ይኖረዋል:: በተመሳሳይ ትምህርትን በአግባቡ መጠቀም ከተቻለና ውጤታማ የትምህርት ሥርዓትን መከተል ከተቻለ የአገር ካስማን በማጽናት በተለያዩ ዘርፎች ቀዳሚና ተጠቃሽ ያደርጋል::

በትምህርት የታገዘ ማሕበረሰብ አምራችና ውጤታማ በመሆን አገር እንድትቀጥል ዋስትና የሚሰጥ በመሆኑ ደግመን ደጋግምን ለትምህርት ጥራት ዋጋ መስጠት ይጠበቅብናል:: ለትምህርት የተሰጠው ዋጋ በዕውቀት ላይ የተመሠረተና ሁሉን አቀፍ ዕድገት ማምጣት የሚያስችል እንዲሆንም የትምህርት ስርዓታችን በሁለንተናዊ መንገድ መመርመር ወሳኝ ነው::

# “በሩብ ዓመቱ ኢትዮጵያ ስኬታማ የሁለትዮሽና የባለብዙ ወገን የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ አከናውናለች”

- አምባሳደር መለስ አለም
የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- በሩብ ዓመቱ ኢትዮጵያ ስኬታማ የሆነ የሁለትዮሽና የባለብዙ ወገን የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ ማከናወኗን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር መለስ አለም አስታወቁ።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ መለስ ዓለም ለሀገር ውስጥና ለውጭ ሀገር መገናኛ ብዙኃን በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ እንደገለጹት፤ የ2016 ዓ.ም የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ አላማ ወደ መደበኛው የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ መመለስና አጋሮችን ማብዛት ነበር።

ባለፉት ሁለት ዓመታት የነበረው የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ ወዳጅ የማብዛት፣ ጠላት የመቀነስ፣ የማስገንዘብ፣ የማለዘብና ተደራሽ መሆን ነበር ያሉት አምባሳደር መለስ፤ 2016 ዓ.ም በአንደኛ ሩብ ዓመት ውስጥ በባለብዙ ወገንና በሁለትዮሽ ዲፕሎማሲ ላይ ትኩረት ሰጥቶ በመስራት የዲፕሎማሲውን እንቅስቃሴ መልከ ብዙና አካታች የማድረግ ሥራ ተሰርቷል ብለዋል።

በሩብ ዓመቱ ኢትዮጵያ ስኬታማ የሆነ የሁለትዮሽና የባለብዙ ወገን ዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ አድርጋለች ያሉት አምባሳደሩ፤ ከተለያዩ ሀገራትና ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር የነበሩ ሥራዎች ውጤታማ ነበሩ ብለዋል።

እንደ አምባሳደር መለስ ገለጻ፤ በሩብ ዓመቱ የተከናወኑ ስራዎች የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ያስከበሩና ያረጋገጡ ናቸው። ለዳግም ግንባታና ለመልሶ ማቋቋም እንቅስቃሴ የሚያስፈልጉ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የዲፕሎማሲ ድጋፍ የተገኘበት ነው። ለዚህም የባለብዙ ወገንና የሁለትዮሽ ዲፕሎማሲን በስፋት ተጠቅማለች።

አምባሳደር መለስ እንዳሉት፤ ጠላትን ከመቀነስና ብሔራዊ ጥቅሞችን ከማረጋገጥ አንጻር ባለፉት ሶስት ወራት ውጤታማ የዲፕሎማሲ ሥራ ተሠርቷል። በበጀት ዓመቱ የምንከተለው ስትራቴጂ ዲፕሎማሲውን መልከ ብዙ ማድረግ ነው። ከሀገሮች ጋር የነበረን እንቅስቃሴ ተሻሽሏል። ከአሜሪካና ከአውሮፓ ኅብረት፣ ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት፤ ከቡድን 77 እና ከሌሎች ጋር የነበሩን የዲፕሎማሲ መስተጋብሮች ብዙ ውጤት እያስገኙ ናቸው።

ከአሜሪካ መንግሥት ጋር በኢንቨስትመንት፣ በንግድና የልማት ትብብር ጉዳዮች፤ በዲሞክራሲ፣ በሰብዓዊ መብቶችና በመልካም አስተዳደር እና በመከላከያና በፀጥታ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ምክክሮች እየተካሄዱ መሆኑን የጠቀሱት አምባሳደር መለስ፤ ይህም የሁለቱን ሀገራት የዲፕሎማሲ ግንኙነት ወደ ነበረበትና የተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር የሚጠቅም ነው ብለዋል።

ከአውሮፓ ኅብረት ጋር ያለው የዲፕሎማሲ ቋንቋ ተቀይሯል ያሉት አምባሳደር መለስ፤ አሁን ንግድ፣ ኢንቨስትመንት፣ አጋርነትና በጋራ ስለ መስራት ውይይቶች አሉ። ድጋፎች እየተደረጉ ነው። ከኢትዮጵያ አልፎ በአፍሪካ ቀንድ ያሉ ችግሮች እንዲፈቱ ኢትዮጵያ ኃላፊነቷን መወጣት አለባት እያሉ ነው ሲሉም ገልጸዋል።

አምባሳደር መለስ እንደገለጹት፤ ከአውሮፓ ኅብረትና አባል ሀገራት ጋር ያለው ግንኙነት ለውጥ የታየበት ነው። ከአየርላንድ ጋር የነበረው የዲፕሎማሲ ሁኔታ ወደነበረበት እንዲመለስ በነሱ በኩል ፍላጎት ታይቷል። ከዲፕሎማሲ አንጻር ኢትዮጵያ ወደ ከፍታ በመምጣትና ተጽዕኖ በመፍጠር ብሔራዊ ጥቅሟን ለማረጋገጥ ብዙ ሥራ እየተሠራ ነው።

እንደ አምባሳደር መለስ ማብራሪያ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ኤምባሲ ለመክፈት የጠየቁ ሀገሮች ብዙ ናቸው፤ በ2016 ብቻ ክሮሽያ፤ ኮሎምቢያ፣ ኒካራጓና ሌሎች ሀገራት ጠይቀዋል። በአንድ ወቅት ኤምባሲ ያላቸው ሀገራት ስጋት ነበራቸው፤ አሁን የስጋት ምዕራፍ መዘጋቱን ያመለክታል። ይህ ትልቅ ትርጉም ያለውና የኢትዮጵያን የዲፕሎማሲ ማዕከልነትና መናኸሪያነት የሚያጸና ነው።

በርካታ ሀገራት ኢትዮጵያ ውስጥ ኤምባሲ በመክፈት ሌሎች ሀገሮችን መሸፈን ይቻላል ብለው ያምናሉ ያሉት አምባሳደር መለስ፤ በኢትዮጵያ በኩል የሚፈለገው ለማዕከልነት የሚሆን መዲና መፍጠር፣ የተሻሉ አገልግሎቶችን መፍጠር፣ ጸጥታውን የተሻለ ማድረግና እንግዳ ተቀባይነትን ከቃል በዘለለ በተግባር ማሳየት ነው ብለዋል።

## ዲጂታል ኢትዮጵያን...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ስትራቴጂው የተቀረፀው፣ በተጨባጭ ሀገራዊና ዓለማዊ ሁኔታዎች ምንድን ናቸው? ያሉት ተሞክሮዎችስ ምን ያሳያሉ? በሚሉት ነጥቦች ላይ ተመርኩዞ ነው። ኢትዮጵያ ከነበረችበት ሁኔታ ተነስታ በ2025 ዲጅታል ኢኮኖሚ እንዲኖራት መሰረት የሆኑ ነገሮችን መገንባትም ዓላማው አድርጓል።

ስትራቴጂው ዲጂታል ኢኮኖሚ ለመገንባት መሰረታዊ ናቸው የሚላቸውን ጉዳዮች አስቀምጧል የሚሉት ዶክተር አብዮት፣ የመጀመሪያው የመሰረተ ልማት ግንባታ መሆኑን ይጠቅሳሉ። የመሰረተ ልማት ግንባታው በዋናነት ሁለት ጉዳዮችን እንደሚመለከትና አንዱ የቴሌኮም መሰረተ ልማት መሆኑን በማውሳት፤ የቴሌኮም ዘርፉን ለማሳደግ የተወሰነው መሰረታዊ የሆነ የፖሊሲ ለውጥ በማምጣት በሀገራችን የቴሌኮሙን ዘርፍ “ሊብራላይዝ” የሚያደርግ እንደሆነ ያነሳሉ። በዘርፉ አዳዲስ ተዋንያን እንዲገቡና በውድድር ላይ የተመሰረተ እንዲሆን በማስቻልም መሰረተ ልማቱ የተሻለ ደረጃ ላይ የማድረስ ስራዎች በተሳካ ሁኔታ መካሄዳቸውን ያስረዳሉ። ሌላኛው ቁልፍ ጉዳይ የሆነው የኃይል መሰረተ ልማት ላይም ስራዎች እየተሰሩ መሆናቸውን በማንሳት ዲጂታላይዜሽን ያለ ኃይል ሊታሰብ እንደማይችል ይገልጻሉ።

ዶክተር ዐቢዮት እንደሚያስረዱት ዲጂታል ኢኮኖሚ ለመገንባት ሁለተኛው መሰረታዊ ጉዳይ የዲጂታል አስቻይ ሥርዓቶች መኖር ነው። እነዚህ የዲጂታል አስቻይ ሥርዓቶች ሦስት ናቸው። አንደኛው ዲጂታል መታወቂያ ነው። በዲጂታል ዓለም ኢኮኖሚ ሲገነባ በዋናነት ግንኙነቶች ቀጥታ (ኦንላይን) ነው የሚሆኑት። በቀጥታ የሚደረግ ግንኙነት ደግሞ ማንነትን ማረጋገጥ ይፈልጋል። ሁለተኛው ዲጂታል የክፍያ ሥርዓት ነው። ዲጂታል ኢኮኖሚ ያለዲጂታል ክፍያ ምንም ሊሠራ ስለማይችል ክፍያዎች ዲጂታል መሆን አለባቸው። በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ ደኅንነት መረጋገጥ አለበት። እነዚህ የዲጂታል ኢኮኖሚ አስቻይ ሥርዓቶች በስትራቴጂው ዘመን ውስጥ እንዲሟሉ ለማድረግ እየተሠራ ነው።

ዲጂታል መታወቂያ ከፓይለትነት ወጥቶ አሁን ወደ ሙሉ ትግበራ እየተሸጋገረ ነው። የዲጂታል ክፍያም የሚያስፈልጉት የህግ ማዕቀፎች ተዘጋጅተውለት በርካታ ተዋንያኖች ወደዘርፉ እንዲገቡ ተደርጎ በተሳካ ሁኔታ እየሄደ ይገኛል። በደኅንነት (ሴኪዩሪቲ) ላይም በጥብቅ ሁኔታ እየተሠራ ይገኛል።

ከዲጂታል አስቻይ ሥርዓቶች ቀጥሎ በስትራቴጂው በሦስተኛ ደረጃ የተቀመጠው ዲጂታል “ኢንተራክሽን” ነው። ጉዳዩ “ኢ-ኮሜርስን” እና “ኢ-ገቨርንመንት” ን የሚመለከት ሆኖ ለማሳለጥ በስፋት የተሄደበት መስክ ነው። ለዘርፉ መሰረት የሆኑት ዲጂታል ገበያው፣ ሎጂስቲክሱ እና የክፍያ ሥርዓት እንዲመቻቹና በመካከላቸው ያለው ግንኙነት የተሳለጠ እንዲሆን በርካታ ሥራዎች መሰራታቸውን ይገልጻሉ።

አራተኛው መሰረታዊ ነገር አጠቃላይ ዲጂታል ኢኮሲስተሙን ማልማት ነው። ሰዎች በዲጂታል ኢኮኖሚ ውስጥ አገልግሎቱን ለመስጠትም ሆነ ለመገልገል የዲጂታል ክህሎት ሊኖራቸው እንዲችሉ የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ ነው።

አማካሪው እንደሚናገሩት በአንድ ሀገር ውስጥ የዲጂታል ኢኮኖሚ ለመገንባት ቁልፍ ሚና የሚጫወተው የግል ዘርፉ ነው። የግል ዘርፉ በዋናነት ሃሳብ ላይ ተመስርቶ ወደተግባር እንዲመጣ ለማድረግ ሁሉን አቀፍ ስታርትአፕን ማበልጸግ ማዕከል ተደርጎ ሲሰራበት ቆይቷል። ዲጂታል ኢኮኖሚ የሚፈልጋቸው ራሳቸውን የቻሉ የሕግ ማዕቀፎች አሉ። በተመሳሳይ መልኩ ደግሞ አሁን ሥራ ላይ ካሉት አሠራሮች የተወሰኑትን ለዲጂታል ኢኮኖሚው በሚመች መልኩ የማስተካከል ሥራ እየተሠራ ነው።

ወደ ዲጂታል ኢኮኖሚ የሚደረገው ጉዞ በስትራቴጂው መሰረት በጥሩ ሁኔታ እየሄደ ነው የሚሉት ከፍተኛ አማካሪው፣ በሂደቱ ከመንግሥት የሚጠበቀው እንደ አንድ ተዋናይ ሁኔታዎችን ማመቻቸት መሆኑን በመግለጽ ትልቁ ሚና የሚጠበቀው ከግል ዘርፉ መሆኑ ላይ አጽንኦት ይሰጣሉ። በዚህም መሰረት ባለፉት ዓመታት ውስጥ በርካታ የግል ተቋማት ወደዚህ ዘርፍ ገብተው እየሠሩ መሆናቸውን ይናገራሉ።

የዲጂታል ስትራቴጂ ተነጥሎ ብቻውን ሊቆም የማይችል በመሆኑ ከሀገሪቷ የልማት ስትራቴጂ ጋር እንዲጣመር መደረጉን የሚጠቅሱት ዶ/ር ዐቢዮት፣ በሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ አጀንዳና በ10 ዓመቱ ትኩረት የተሰጣቸው የኢኮኖሚ ዘርፎች በስትራቴጂው ቅድሚያ እንደተሰጣቸው ይገልጻሉ።

የዘርፉ ባለሙያ የሆኑት አቶ በቃሉ በፈቃዱ፤ ኢትዮጵያ ወደ ዲጂታል ዓለም የምታደርገው ጉዞ በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ለውጦች የታዩበት መሆኑን ይጠቅሳሉ። ወደ ታች ሲወረድ ጉዞ አንዳንድ ውስንነቶች እንዳሉበት የሚገልጹት ዳይሬክተሩ “በተቋማት የኢንፎርሜሽን መሰረተ ልማት ዝርጋታ በስፋት አልተከናወነም። በዚህ ምክንያት አሠራርን የሚያዘምን ሥርዓት (ሲስተም) ሲወርድ ትግበራው አስቸጋሪ ይሆናል። ሕዝባችንም ለዲጂታል ቴክኖሎጂ ያለው ግንዛቤም ብዙ ሥራ የሚፈልግ ነው። አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ተቀብሎ አብሮ በመጓዝ ረገድ ዝግመቶች አሉ ይላሉ።

በየተቋማቱ ያሉ አመራሮች ከቴክኖሎጂ ጋር በተያያዘ ያላቸው ግንዛቤ ደካማ ነው። ለምሳሌ አነስተኛ መጠን ላለው የቴክኖሎጂ እቃ በመቶ ሺዎች ብር ዋጋ ሲተመንለት ተቀብለው ግዢ ለመፈጸም ፈቃደኛ አይሆኑም። “ዘመኑ የደረሰባቸው የቴክኖሎጂ ውጤቶች በመጠናቸው አነስተኛ የሆኑና ብዙ ሥራዎችን የሚያከናውኑ ናቸው። የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ባለሙያዎች የግዢ ፍላጎታቸውን ካሳወቁ በኋላ አመራሮች ይሄን ሁሉ ብር አውጥተን ግዢ አንፈጽምም ስለሚሉ ለማሳመን ትልቅ ትግል ይገጥማቸዋል” በማለት በቀጣይ ችግሮቹን ለመቀነስ በትኩረት መሠራት እንዳለበት ያሳስባሉ።

ዶክተር ዐቢዮትም አቶ በቃሉ ያነሷቸው ውስንነቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ ጠቅሰው፤ መፍትሄው እየተሰሩ ያሉ ሥራዎችን አጠናክሮ መቀጠል መሆኑን ይገልጻሉ። “በዋናነት ዕድሉን ተቀምጦ ስለማናገኘው ራሳችን ልንፈጥረው ነው የሚገባን። በመሰረቱ የዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂ ዓላማ ዕድል እንዲፈጠር ማድረግ ነው። ለምሳሌ ለዲጂታል ኢኮኖሚ መሰረት የሆኑትን ነገሮች ካላለማናቸው በቀር በራሳቸው የምናገኛቸው አይደሉም” በማለት ዲጂታል ኢኮኖሚን መገንባት የሚያስችል መደላድል ለመፍጠር እየተደረገ ያለው እንቅስቃሴ እየጎለበተ መሄድ እንዳለበት ይጠቁማሉ።

ዲጂታል ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ በጥራትና በፍጥነት እየተደረገ ያለው አስደናቂ ጉዞ የነገዋን ኢትዮጵያ መልክ የሚቀይር ይሆናል። በጥቅሉ ወጪን በመቆጠብ፣ የፋይናንስ አደጋ ተጋላጭነትን በመቀነስ፣ የጥሬ ገንዘብ ዝውውርን በማስቀረት፣ የዲጂታል ግብይት ተደራሽነትን በማስፋፋትና ግልጽነት ያለው ፈጣን አገልግሎት በመስጠት ሁለንተናዊ እድገት ማስመዝገብ የሚቻልበትን ዕድል ይፈጥራል ተብሎ ይጠበቃል።

## “ግብር በመክፈል ለሕዝብና...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

አንዱ የአረበኝነት መገለጫ ነው። በሀቀኝነት ግብር በመክፈል ለሕዝብና ለመንግሥት መታመን አረበኝነት ነው።

በቁጥር አነስተኛ የሆነ አርበኞችን እውቅና መስጠትና መሸለም ትልቅ ጉዳይ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ባለጸጎች ሀብት ማፍራት ብቻ ሳይሆን ግብር በመክፈል ታማኝ እንደሆኑ ሁሉ ሀገር በማጽናት ረገድ የበኩላቸውን ሚና መወጣት እንዳለባቸው ገልጸዋል።

በአባቶቻችን ልፋትና ጥንካሬ ኢትዮጵያ የፖለቲካ ሉዓላዊነታችንን አስጠብቃለች። ምንም ዓይነት ጫና የለባትም ባይባልም የፖለቲካ ሉዓላዊነት ስለሌለባት የራሷን ሕጎች ማውጣትና ማስፈጸም የምትችል ሀገር መሆኗን አመልክተዋል።

ሁለተኛው የፖሊሲ ሉዓላዊነት ነው። ለእኛ የሚያስፈልጉንን ፖሊሲዎች ለማውጣት ነፃነት ያለን ሀገር ነን። ነገር ግን ኢትዮጵያ በሌሎች ሀገራት ያልተገዛች ነፃ ሀገር ናት ብለን ብንናገርም ዛሬም ድረስ የምግብ ሉዓላዊነት ማረጋገጥ አልቻልንም ነው ያሉት።

በምግብ ራሳችንን መቻል ካልቻልን ፖሊሲያችንና ፖለቲካችን የተሟላ ለማድረግ አንችልም ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ባለሀብቱ ግብርን በታማኝነት ከመክፈሉ ጎን ለጎንም በምግብ ራስን ለመቻል በሚደረገው ጥረትም የበኩሉን ሚና መጫወት እንደሚኖርበት አመልክተዋል።

የምግብ ሉዓላዊነት ለኢትዮጵያ ያስፈልጋል ብቻ ሳይሆን መሳካት ያለበት ተግባር መሆኑን ጠቁመው፤ ሰፊ መታረስ የሚችል መሬትና የሰው ሀብት ያለ በመሆኑ በምግብ ራስን በመቻል ሦስተኛውን ሉዓላዊነት ማስከበር ያስፈልጋል ብለዋል።

አራተኛው የበጀት ሉዓላዊነት መሆኑን የጠቀሱት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ ሥራ ለመሥራት እንደ መንግሥት ስናቅድ ከግብር የሚገኘውን ገቢ ሲያጥር የተቀረውን በብድርና በልመና እናሟላለን። ከዚህ መነሻነት የበጀትን ነፃነት ማረጋገጥ ረገድ የተሸለማችሁ ታማኝ ግብር ከፋዮች ሚናችሁ ከፍተኛ ስለሆነ ይህን አጠናክራችሁ መቀጠል ይኖርባችኋል ብለዋል።

የሉዓላዊነትን ዘውግ በተሟላ ደረጃ ለመጎናጸፍ እንደ መንግሥት ግልጽ ፖሊሲ መኖሩን አውስተው፤ የግሉ ሴክተር አቅም በፈቀደ መንገድ የመደገፍ ሥራ እየተሠራ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

ለአብነትም ከለውጡ በፊት በመንግሥትና በግል ባንኮች ተቀማጭ ከሆነው ሀብት ከ75 በመቶ በላይ ብድር የሚሰጠው ለመንግሥት እንደነበር አስታውሰው፤ ከለውጡ በኋላ ለግሉ የሚሰጠው የብድር መጠን በእጅጉ እያደገ መሄዱን ገልጸዋል። ዘንድሮ ብቻ ለግሉ ዘርፍ 84 በመቶ ብድር አቅርቦት ያገኘ መሆኑን ጠቅሰዋል። ይህም በሀገራችን ዕድገት ላይ ከፍተኛ ለውጥ አሳይቷል ነው ያሉት።

የሚሰበሰበው ገቢ እያደገ ቢሆንም በሚፈለገው ልክ እንዳልሆነ ገልጸው፤ የሚሰበሰበውን ገቢ ለማሳደግ የታክስ መሠረቱን ማስፋትና ሕገ ወጥ ንግድን ወደ ሕጋዊ ሥርዓት ማስገባት ይኖርብናል ነው ያሉት።

ከእናንተ የምንሰበስበውን ገንዘብ በመሠረተ ልማት ግንባታዎች እያዋልነው እንገኛለን ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ 24 ሺህ ኪሎ ሜትር ኮንክሪት አስፋልት መንገድ እየገነባን ነው፤ እርሻ ምርታማነት አሳድገናል፤ የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎችን በስፋት እየገነባን እንገኛለን ሲሉ ለአብነት ጠቅሰዋል።

በቀጣይ አምስት ጉዳዮች ላይ አተኩረን መሥራት ይኖርብናል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ አንደኛው የኩባንያዎች ብክነትን በመቀነስ ሀብትን ማሳደግ እንደሚያስፈልግ፤ የገቢ መሠረትን ማስፋት እንደሚገባ፣ ሌብነት፣ ኮንትሮባድንና ሕገወጥነትን ማስወገድ እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

ሌላው ሕጋዊነትን፣ ሥርዓትንና ተገማችነትን ማካተት እንደሚገባ፣ አሠራርን ማዘመንና ግልጽ ማድረግ እንደሚኖርባቸው አሳስበዋል።

በመንግሥት በኩልም አሠራርን ለማዘመንና የተሳለጠ ለማድረግም መንግሥት በቅርቡ ጠንከር ያለ ሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም እንደሚጀምር ይፋ አድርገዋል።

ሰላምን ከማጽናት አኳያም ኢትዮጵያ ብዙ የውጭና የውስጥ ጠላት ያላት ሀገር ስለሆነች ነቅተን ካልጠበቅናት ሀገር አልባ እንሆናለን ነው ያሉት።

በ12 የተለያዩ መስፈርቶች የተመረጡ 500 ታማኝ ግብር ከፋዮች ምሥጋና እና ዕውቅና ተሰጥቷቸዋል። ከእነዚህ ውስጥ 50 ግብር ከፋዮች በፕላቲኒየም፣ 150 በወርቅ፣ 300 በብር ደረጃ ምስጋና እና ዕውቅና የተሰጣቸው ሲሆን 14 ግብር ከፋዮች በመርሀ ግብሩ ልዩ ሽልማት ተበርክቶላቸዋል።

## “ዩኒቨርሲቲው የመምህራንን ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ትኩረታቸውን የሚያደርጉት ህንፃ መገንባት ላይ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲው ይህን አካሄድ በመቀየር ዕውቀት ላይ ትኩረት አድርጎ መስራት ይኖርበታል ብለዋል።

ፕሮፌሰር ብርሃኑ እንደገለጹት፤ በሀገሪቱ የተማሩ ሰዎች ቁጥር በርካታ ቢሆንም ከጥራት አንጻር ሲታይ ክፍተቶች ይታያሉ። በመሆኑም የኮተቤ ዩኒቨርሲቲ ብዛት ላይ ሳይሆን ጥራት ላይ ትኩረት አድርጎ መስራት ይኖርበታል።

ትምህርት ሚኒስቴር በዘንድሮ በጀት ዓመት የመምህራን ጥራት ላይ ትኩረት አድርጎ እንደሚሰራ የጠቆሙት ሚኒስትሩ፤ ለሚኒስቴሩ የሥራ ስኬት የዩኒቨርሲቲው አስተዋጽኦው የጎላ መሆኑን አመላክተዋል።

የኮተቤ ዩኒቨርሲቲ የበቁ መምህራንን ለማፍራት በሚያደርገው ጥረት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርግ ገልጸዋል።

የትምህርት ሚኒስትር ዴኤታ ሰለሞን አብረሃ (ዶክተር) በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ በአሁኑ ወቅት ዓለም ለትምህርት ልዩ ትኩረት በመስጠት እየሠራ ይገኛል።

የሀገሪቷን የትምህርት ዘርፍ ለማሻሻል ባለፉት ዓመታት መንግሥት የተለያዩ ሥራዎችን ሲሠራ መቆየቱን ዶክተር ሰሎሞን አስረድተዋል።

በሀገሪቱ የተማረ ሰው ኃይል ከ32 ሚሊዮን ማለፉን ጠቁመው፤ 51 የመንግሥት እና አምስት የግል ዩኒቨርሲቲዎች እንዲሁም በርካታ የግል ኮሌጆች አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን አስታውቀዋል።

የትምህርት ዘርፉን በማስፋት ረገድ ስኬታማ የሚባሉ ዓመታት ቢኖሩም፤ የሀገሪቱ የትምህርት ጥራት ሲገመገም በሁሉም ዘርፍ ማሽቆልቆል ይታያል ሲሉ አስረድተዋል።

ትውልዱ ያገኘውን ፀጋ ለሀገር ግንባታ እንዲያውልና ሀገር ወዳድ በመሆን ያለውን አቅም ለሕዝብ እንዲያበረክት የሚደግፍ መምህር ያስፈልገዋል ያሉት ዶክተር ሰለሞን፤ ኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ በዚህ ረገድ ጠንካራ ሥራ ማከናወን ይጠበቅበታል ሲሉ ገልጸዋል።

መንግሥት ጥራቱን የጠበቀ የትምህርት ሥርዓት እንዲኖር የተለያዩ ሪፎርሞችን በማስጀመር እየሠራ ይገኛል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ የኮተቤ ትምህርት ዩኒቨርሲቲ መወለድ አንዱ የለውጡ አካል ነው ብለዋል።

# ‹‹ተስፋ አዲስ›› - የካንሰር ሕሙማን ሕፃናት የሕይወት ተስፋ

**አንተነህ ቸሬ**

በኢትዮጵያ ገና በለጋነታቸው የካንሰር ተጠቂ የሆኑ ሕፃናት ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ መጥቷል:: ኅብረተሰቡ ስለካንሰር ሕመም ያለው የተሳሳተ ግንዛቤ፣ ሕክምናው እንደልብ አለመገኘቱ እንዲሁም በጥቂት ተቋማት ውስጥ ብቻ የሚሰጡት ሕክምናዎችም ውድ መሆናቸው የችግሩን ክብደት የበለጠ ፈታኝ አድርጎታል:: በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ወገኖች ደግሞ በዚህ ችግር ምክንያት ለበለጠ አስከፊ መከራ ተዳርገዋል:: ጉዳዩ ያሳሰባቸው ግለሰቦችና ተቋማትም ይህን አስቸጋሪ ሁኔታ ለመቀየር የተለያዩ ጥረቶችን አድርገዋል፤ እያደረጉም ናቸው::

ለካንሰር ታካሚ ሕፃናት የሚቀርበውን ሕክምና ጥራቱን በማሻሻል የሕፃናቱን ሕይወት በማዳን እና ወላጆች ለልጆቻቸው የተሻለ እንክብካቤ እንዲያደርጉ ማብቃት እንዲሁም የሕክምና ተቋማትን የሕፃናት ካንሰር ሕክምና ክፍል አቅም በመገንባት ሕሙማኑ የተሻለ አገልግሎት እንዲያገኙ የማስቻል ዓላማን ይዞ የተቋቋመው ‹‹ተስፋ አዲስ ፓረንትስ ቻይልድሁድ ካንሰር ድርጅት›› (Tesfa Addis Parents Childhood Cancer Organization) የችግሩን አስከፊነት ለመቀነስ ከተደረጉ የበጎ አድራጊ ዜጎች ጥረቶች መካከል ተጠቃሹ ነው::

የ‹‹ተስፋ አዲስ ፓረንትስ ቻይልድሁድ ካንሰር ድርጅት›› ሥራ አስኪያጅ ወይዘሮ ሳራ ኢብራሂም እንደሚናገሩት፣ ድርጅቱ የተመሠረተው በኅዳር 2005 ዓ.ም ነው:: የድርጅቱ መሥራቾች ደግሞ ልጆቻቸውን አሳክመው ያዳኑና ልጆቻቸው በሕክምና ላይ የነበሩ ወላጆች እና የሕክምና ባለሙያዎች ናቸው:: ስለካንሰር ታማሚዎች በኅብረተሰቡ ዘንድ ያለው ግንዛቤ ዝቅተኛ በመሆኑ ግንዛቤውን ከመቀየር ጀምሮ የካንሰር ታማሚዎች ተገቢውን ሕክምና እንዲያገኙ ማድረግ አስፈላጊ ተግባር ስለነበር የ‹‹ተስፋ አዲስ›› ምሥረታ እውን ሆነ::

‹‹ድርጅቱ የተመሠረተው ልጆቻቸው በካንሰር ታመውባቸው በሕክምና የዳኑላቸው ወላጆች ትብብር ሲሆን፣ ወላጆቹም ሊተባበሩ የቻሉት ‹ልጆቻቸው ከዳኑ እኛ ደግሞ ለቀሩት የካንሰር ታካሚ ሕፃናት የበኩላችንን አስተዋጽዖ ማድረግ አለብን› ከሚል ቅን መንፈስ ተነሳስተው ነው›› በማለት ወይዘሮ ሳራ ስለድርጅቱ አመሠራረት ያስታውሳሉ::

ድርጅቱ የተቋቋመው የካንሰር ታማሚ ሕፃናት በሆስፒታል ቆይታቸው በቂ ሕክምናና እንክብካቤ የሚያገኙበት ሁኔታ እንዲፈጠር እና በቀጣይነት ሕክምናቸውን እንዲከታተሉ ጥረት ለማድረግ ታስቦ ነው:: በካንሰር የተያዙ ልጆች ተገቢውን ሕክምናና እንክብካቤ አግኝተው ከካንሰር ነፃ የሆነ ሕይወት እንዲመሩ የማድረግ ራዕይ ያለው ድርጅቱ፣ ተልዕኮው ወላጆችን ማዕከል ባደረገ እንቅስቃሴ ጥራቱን የተጠበቀ የሕክምና አገልግሎትና ክትትል በማድረግ የታካሚ ልጆች ከካንሰር ነፃ የመሆን እድልን መጨመር ነው::

‹‹ተስፋ አዲስ›› ከአዲስ አበባ በተጨማሪ በጎንደርና በጅማ የታካሚ መርጃ (የማደሪያ) ማዕከላት አሉት:: ድርጅቱ የካንሰር ታማሚ ሕፃናትን የመርዳት ሥራውን የሚያከናውነው ከመንግሥት የጤና ተቋማት ጋር በመተባበር ሲሆን ተቋማቱ ጥቁር አንበሳ፣ ቅዱስ ጳውሎስ፣ የጅማ ዩኒቨርሲቲ፣ የጎንደር ዩኒቨርሲቲ እና ዓይደር ሆስፒታሎች ናቸው:: ድርጅቱ በዚህ ተግባሩ የካንሰር ታማሚዎቹ ሕክምና እንዲያገኙ ያደርጋል:: ከዚህ በተጨማሪም ተቋሞቹ ያሉባቸው የተለያዩ ክፍተቶች እንዲሟሉ እና ለታካሚዎቹም በቂ አገልግሎት እንዲሰጡ ድጋፍ ያደርጋል:: ለአብነት ያህል በቅርቡ በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሕክምና ኮሌጅ፣ በእናቶችና የሕፃናት ሕክምና ማዕከል ውስጥ የሚገኘው የሕፃናት ካንሰር ሕክምና ክፍል ለሕክምና አስፈላጊ በሆኑ ግብዓቶች እንዲሟላና እንዲደራጅ አድርጓል:: ከዚህ ባሻገርም በክፍሉ ከተመደቡት የሆስፒታል ሕክምና ባለሙያዎች በተጨማሪ ድርጅቱ አንድ የሥነ ልቦና ባለሙያና አንድ መረጃ የሚያጠናቅር ሠራተኛ መድቧል::

የሕክምና አገልግሎቱን የሚያገኙት ልጆች ወደ ተቋሙ የሚመጡበት የራሱ የሆነ አሠራር አለው:: ድርጅቱ ዕገዛና ድጋፍ የሚሹ ሕፃናትን የሚያገኘው ድርጅቱ የድጋፍ አገልግሎት በሚሰጥባቸው ሆስፒታሎች ውስጥ የመደባቸው የሥነ ልቦና ባለሙያዎች ከሆስፒታሉ ሐኪሞች ጋር በመሆን አጣርተው በሚልኩት መረጃ መሠረት ነው:: ‹‹አዝላን›› ፕሮጀክትን (Aslan Project) ጨምሮ በርካታ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ለ‹‹ተስፋ አዲስ›› የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋሉ:: ድርጅቱ በአሁኑ ወቅት ከ600 በላይ ለሆኑ ሕፃናትና ወላጆች ድጋፍ እያደረገ ይገኛል::

**ካንሰር** በጊዜ ከተደረሰበት የመዳን ዕድሉ በጣም ከፍተኛ በመሆኑ ወላጆች ይህንን ተገንዝበውና ተስፋ ሳይቆርጡ ልጆቻቸውን ከማሳከም ወደ ኋላ ማለት የለባቸውም

ወይዘሮ ሳራ እንደሚያብራሩት፣ ድርጅቱ የካንሰር ሕሙማን ሕፃናት ሕክምና እንዲያገኙ ከማድረግ በተጨማሪ ከሕክምናው ጋር ተያያዥ የሆኑ አገልግሎቶችንም ለታካሚዎቹ ያቀርባል:: እነዚህ አገልግሎቶችም የምግብ፣ የመጠለያ/ማደሪያ፣ የትራንስፖርት፣ የአልባሳት፣ የክህሎት ሥልጠና፣ የንጽሕና መጠበቂያ እና የሥነ ልቦና ድጋፎች ናቸው::

‹‹ድርጅቱ ለሕፃናቱና ለወላጆችና ማኅበራዊ እና ሥነ-ልቦናዊ ድጋፎችን ያደርጋል:: ለታካሚዎችና ለወላጆች የምግብ አቅርቦት፣ ከክልሎች ለሚመጡና አቅም ለሌላቸው ታካሚዎችና ወላጆች የትራንስፖርት እና የማደሪያ አገልግሎት ይሰጣል፤ ለታካሚዎች የትምህርት ቁሳቁስ ድጋፍ ይደረጋል፤ በተለያዩ ዘርፎች ለወላጆች የሚሰጣቸው ሥልጠናዎችም አሉት፤ ለታካሚዎችና ለወላጆች የምክር አገልግሎት ይሰጣል:: በተጨማሪም ድርጅቱ የሕፃናት ካንሰር ሕመም እንደሌሎቹ ሕመሞች ሊከሰት እንደሚችል፣ በጊዜው ከተደረሰበትና ከታከመ ግን የሚድን እንደሆነ ለኅብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን ይሠራል›› ይላሉ::

የመጠለያ/ማደሪያ አገልግሎቱ ልጆቻቸውን ለማሳከም ወደ ማዕከላቱ የሚመጡ ወላጆች በቅርበት ሆነው ለልጆቻቸው ድጋፍ እንዲያደርጉ እድል ይሰጣቸዋል:: የመጠለያ አገልግሎቱ የምገባ፣ የጤና/ጽዳት፣ የትራንስፖርት (ወደ ሕክምና ተቋማት) እና የሕፃናት መዝናኛ አገልግሎቶችንም ያካተተ ነው:: በድርጅቱ የሚሰጠው ታካሚ ሕፃናትን ወደ ሕክምና ተቋማት የማድረስና ወደ ማዕከሉ የመመለስ አገልግሎት ሕፃናቱ ለአላስፈላጊ እንግልት እንዳይዳረጉ እንዲሁም ለኢንፌክሽን እንዳይጋለጡ ያደርጋቸዋል::

በሕፃናት ካንሰር ሕመም ምንነት፣ በሕክምና ዘዴዎቹ፣ በጤና አጠባበቅና በአመጋገብ ሥርዓት ላይ አተኩሮ የሚሰጠው የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርትና የሥነ ልቦና ድጋፍና የታካሚ ሕፃናትን ሥነ ልቦና በመገንባት ለመዳን እድላቸው አወንታዊ አስተዋፅዖ ያበረክታል፤ የወላጆችን ግንዛቤ በመጨመር ለልጆቻቸው የሚያደርጉትን እንክብካቤና ድጋፍ በትኩረት እንዲያከናውኑ እና ኅብረተሰቡ ስለችግሩ ያለው አመለካከት እንዲቀየር ያግዛል::

‹‹የካንሰር ሕክምና ረጅም ጊዜ የሚፈጅ ነው:: ሕክምናው በቂ ጊዜ እንደሚፈልግ አስቀድሞ ወላጆችን ማስተማርና ማሳመን ያስፈልጋል:: ከዚህ በተጨማሪም ሕፃናቱ ለረጅም ጊዜ በሕክምና ላይ ሲቆዩ ጫና እንዳይፈጠርባቸው የሥነ ልቦና ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል:: በሥነ ልቦና ዝግጁ ሆነው መታከም ስላለባቸው ድጋፍ የሚያደርጉ ባለሙያዎች አሉ:: ልጆቻቸው ታክመው የዳኑላቸው ወላጆችም ወደ ማዕከሉ እየመጡ "ያስተምራሉ፤ ልምዳቸውን ያካፍላሉ" በማለት ወይዘሮ ሳራ ድርጅቱ ለታካሚዎችና ወላጆች ስለሚያደርገው የሥነ ልቦና ድጋፍ ያስረዳሉ::

‹‹ተስፋ አዲስ›› በሚያከናውናቸው ተግባራት የካንሰር ታማሚዎች፣ በተለይም በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ወላጆች ልጆቻቸው ተገቢውን የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታዎች እየፈጠረ እንደሚገኝና የድርጅቱ የበጎ አድራጎት ተግባራት የብዙዎችን ሕይወት በበጎ መልኩ እንደቀየሩ ወይዘሮ ሳራ ይገልጻሉ::

እርሳቸው እንደሚሉት፤ ድርጅቱ እስካሁን ድረስ ከሦስት ሺ በላይ ሕፃናትን ታድጓል:: ድርጅቱ በገንዘብ ምክንያት የሕክምና አገልግሎቱን ሳያገኙ ለሚሄዱ ሕሙማን በፍጥነት በመድረስ ሕክምና እንዲያገኙ እያደረገ ይገኛል:: የሕክምና አገልግሎቱንም ፈልገው የሚመጡ ሕሙማንን ወላጆቻቸው በፍጥነት ወደ ተቋሙ ካመጧቸው የመዳን ዕድላቸው ሰፊ ሲሆን፣ አንዳንድ ወላጆች ግን ስለበሽታው በቂ ግንዛቤ ስለሌላቸውና ዘግይተው በመምጣታቸው የተነሳ ልጆቻቸው ለከፋ ችግር ሲጋለጡ ይታያል:: እነዚህንም ችግሮች ለመፍታት ተቋሙ የተለያዩ አገልግሎቶችን በመስጠት ሕሙማንን ከበሽታው ሙሉ ለሙሉ እንዲያገግሙ እያደረገ ይገኛል:: በተለይም ደግሞ ከሩቅ ቦታ መጥተው ልጆቻቸውን ለሚያስታምሙ ወላጆች ተቋሙ ከሕክምና ጀምሮ ሌሎች አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታዎችን እየፈጠረ ይገኛል:: በሌላ በኩል ደግሞ ከሌሎች ተቋሞች ጋር ቅንጅት በመፍጠር ሰፊ ሥራዎችን እየሠራ ነው:: ከጤና ሚኒስቴር፣ ከግል ተቋማትና ከኤምባሲዎች ጋር በመተባበር ታካሚዎች የተሻለ አገልግሎት እንዲያገኙ ጥረት እያደረገ ነው:: መንግሥት ለድርጅቱ የተለያዩ ድጋፎችን እያደረገ እንደሚገኝም ይገልጻሉ::

ወይዘሮ ሳራ ድርጅቱ በ11 ዓመታት የሥራ ጉዞው ስላጋጠሙት ችግሮች ሲያብራሩ፣ ‹‹ችግሩ ሰፊ ነው:: የሕክምናው ተደራሽነትም ገና ብዙ ይቀረዋል:: የመድኃኒትና ሌሎች ግብዓቶች ችግሮች አሉ:: መድኃኒትን በተመለከተ መንግሥት በጤና መድን በኩል የሚያቀርበው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አንዳንድ ጊዜ ከውጭ በሚገዛበት ጊዜ ዋጋው በጣም ውድ ይሆናል::››ይላሉ::

እሳቸው እንዳሉት፤ እስካሁን ሕክምናውን የሚሰጡት አምስት ሆስፒታሎች ብቻ ናቸው፤ ሕክምናውን የሚሰጡ ሐኪሞችም በጣም ጥቂት ናቸው:: የሕክምና አገልግሎቱ በሚሰጥበት ጊዜ የራዲዮሽን መትከያ መሣሪያ የሚገኘው ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ላይ ብቻ ነው:: ለሕክምና የሚሆነው ማሽን ሲበላሽ ሕሙማኑ ችግር ላይ ይወድቃሉ:: በቅርቡ ይህ የሕክምና አገልግሎት በጅማ ሆስፒታል በመጀመሩ ችግሩ በተወሰነ መልኩም ቢሆን ሊቀረፍ ችሏል:: ይሁን እንጂ ይህም በቂ አይደለም::

በግንዛቤ ረገድ ያለው ችግርም በቀላሉ የሚታይ አይደለም፤አብዛኛው ሰው ካንሰርን የማይድን ሕመም አድርጎ ይቆጥረዋል:: የካንሰር ሕሙማን ሕፃናት ተገቢውን ሕክምና በወቅቱ ማግኘት ከቻሉ የመዳን እድላቸው ከፍተኛ ነው:: ስለሆነም ‹‹ሐኪሞችን በብዛት ማሰልጠን ይገባል:: የሕክምና ቦታዎች መስፋፋት አለባቸው:: የመድኃኒት አቅርቦትንም መጨመር ያስፈልጋል:: ካንሰር በጊዜ ከተደረሰበት የመዳን ዕድሉ በጣም ከፍተኛ በመሆኑ ወላጆች ይህንን ተገንዝበውና ተስፋ ሳይቆርጡ ልጆቻቸውን ከማሳከም ወደ ኋላ ማለት የለባቸውም ›› በማለትም ይመክራሉ::

‹‹ግለሰቦችና ተቋማት በአጠቃላይ ኅብረተሰቡ ከግንዛቤ ለውጥ ጀምሮ ተጨማሪ ድጋፎችን ካደረገ ከዚህ የተሻለ ለውጥ ማስመዝገብ ይቻላል›› የሚሉት ወይዘሮ ሳራ፣ ‹‹ተስፋ አዲስ›› በቀጣይ ጊዜያት ሥራውን በስፋት በማከናወንና ብዙ የካንሰር ታማሚ ሕፃናትን በመታደግ ችግሩን ትርጉም ባለው መልኩ የመቀነስ እቅድ እንዳለው ገልፀዋል::

ማህበራዊ

# ወጣቶች

## ኮከቦቹ ተማሪዎች

**ክብረአብ በላቸው**

በ2015 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና የተመዘገበው ውጤት ብዙዎችን እያነጋገረ ነው:: ገሚሱ ተማሪውን ሲወቅስ፣ ከፊሉ ደግሞ የትምህርት ሥርዓቱን ያነሳል:: በትምህርት ዘመኑ ለፈተና የተቀመጡት ተማሪዎች 845 ሺህ 188 ሲሆኑ፤ ከነዚህ ውስጥም ከ356 ሺህ 878 የተፈጥሮ ሳይንስ፣ 488 ሺህ 221 የማኅበራዊ ሳይንስ ተፈታኞች ናቸው:: በተፈጥሮ ሳይንስ የማለፊያ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች 22 ሺህ 974፣ በማኅበራዊ ሳይንስ ደግሞ 8 ሺህ 250 ተማሪዎች መሆናቸውን ትምህርት ሚኒስቴር ይፋ አድርጓል::

በተጨማሪም ትምህርት ሚኒስቴር እንዳስታወቀው፤ በ2015 የትምህርት ዘመን የ12ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ብሔራዊ ፈተና ከወሰዱ 845 ሺህ 188 ተማሪዎች ውስጥ 27 ሺህ ተማሪዎች ከ50 በመቶ በላይ በማምጣት የማለፊያ ውጤት ያስመዘገቡ ናቸው።

ፈተና ከወሰዱት አጠቃላይ ተማሪዎች ውስጥ ያለፉት 3.2 በመቶ (3.2%)ብቻ ናቸው:: ተማሪዎች ያስመዘገቡት ውጤት ከባለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር በ0.01 ቀንሷል። በትምህርት ዘመኑ ተማሪዎች ያስፈተኑ ትምህርት ቤቶች 3 ሺህ 106 መሆናቸውን የሚኒስቴሩ መረጃ ያሳያል:: ከእነዚህ ትምህርት ቤቶች ውስጥ 1 ሺህ 328 ትምህርት ቤቶች ደግሞ አንድም ተማሪ ማሳለፍ እንዳልቻሉም ተመልክቷል:: ይህም በመቶኛ ሲታይ 42.8 ከመቶ ትምህርት ቤቶች ምንም ተማሪ ማሳለፍ ያልቻሉ እንደሆነም ተጠቅሷል::

በትምህርት ዘመኑ ከፍተኛ ውጤት ሆኖ የተመዘገበው 649 ሲሆን፤ ይህም ውጤት የተመዘገበው በተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርት ዘርፍ በሴት ተማሪ ነው። ይህን ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገበችው ተማሪ ሃናን ናጂ ትባላለች:: በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኘው ክፋዝ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ የሆነችውን ሃናን ናጂን አግኝተን አነጋግረናታል::

ተማሪ ሃናን እንደነገረችን፤ ከቅድመ መደበኛ ጀምሮ ትምህርቷን የተከታተለችው ክፋዝ ትምህርት ቤት ነው:: እስከ ሰባተኛ ክፍል በነበረው የትምህርት እርከን የደረጃ ተማሪ እንደነበረች ታስታውሳለች:: ይሁን እንጂ በጣም ጎበዝ ከሚባሉ ተማሪዎች መካከል አልነበረችም:: ሰባተኛ ክፍል ስትደርስ ግን ከክፍል አንደኛ መውጣት እንዳለባት ዓልማ ትኩረቷን ትምህርት ላይ አደረገች:: የሚሰጣትን የቤት ሥራ በወቅቱ በመሥራት፣ በክፍል ውስጥም በመከታተልና በጥናትም ጊዜ በመስጠት ከሰባተኛ ክፍል ጀምሮ የአንደኝነቱን ደረጃ ለማንም አሰልፋ ሳትሰጥ እስከመጨረሻው ዘለቀች።

በ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና 100% በማምጣት ነው ወደ ሚቀጥለው ትምህርት ያለፈችው:: በሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ቆይታዋ እንዲሁ ሙሉ ጊዜና ትኩረቷን ለትምህርቷ በመስጠት በክፍል ውጤት 9ኛ ክፍል 97፣ 10ኛ ክፍል 98፣ 11ኛ ክፍል ደግሞ 99 አማካኝ ውጤት በማስመዝገብ ስኬታማ እንደነበረች አስታውሳለች::

የ2015 ብሔራዊ ፈተናንም እንዲሁ በስኬት ለማጠናቀቅ ቀድማ ዝግጅት ማድረጓን የምትገልፀው ሃናን፤ "አስራ አንደኛ ክፍል ከጨረስን በኋላ የአስራ ሁለተኛ ክፍል የክረምት ትምህርት ነበረን ከዛን ጊዜ ጀምሮ ለፈተና እየተዘጋጀሁ ነበር" ትላለች። ባስመዘገበችው ውጤት በራሷ እንደኮራችና ደስተኛም እንደሆነች የምትገልፀው ሃናን፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ ቀዳሚ ውጤት አመጣለሁ ብላ ባትጠብቅም ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ እንደምትችል ግን እርግጠኛ እንደነበረች ተናግራለች።

ሃናን ስለትምህርት ተሞክሮዋ እንዳጫወተችን፤ ወደ ክፍል ከመሄዷ በፊት ቀድማ የማንበብና የመዘጋጀት ልምድ አላት:: ይህ ልምዷ በአጠቃላይ የትምህርት ውጤቷ የተሻለ እንዲሆን አግዟታል:: ሁሉም ተማሪ ጊዜውን በአግባቡ ከተጠቀመበትና ለትምህርቱ ትኩረት ከሰጠ ውጤታማ መሆን እንደሚቻልም ትገልጻለች::

ከፍተኛ ቁጥር ካለው ተፈታኝ መካከል ከፍተኛ ውጤት ማምጣት የተለየ ስሜት እንዳለው የምትናገረው ሃናን፤ ጥረት ከተደረገ ስኬት ላይ መድረስ እንደሚቻል ከራስዋ ተሞክሮ ማግኘቷንም ታስረዳለች::

ተማሪ ሃናን ከሥር ጀምራ ለትምህርት የሰጠችውን ትኩረት በመቀጠል በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ በሚኖራት የትምህርት ቆይታም በስኬት ለማጠናቀቅ መዘጋጀቷን ነው የነገረችን:: ወደፊት በባዮ ሜዲካል የትምህርት ዘርፍ ተመራማሪ የመሆን ፍላጎት አላት::



ሃናን ናጂ፣

> **ተማሪዎቹ አፅንኦት ሰጥተው ያስተላለፉት መልእክትም ተማሪዎች ዋና ሥራቸው ትምህርት መሆኑን ተገንዝበው አልባሌ ቦታ ከመዋል ተቆጥበው ጊዜያቸውን ለትምህርት ማዋል እንዳለባቸው ነው**

በመድኃኒት ልማት ላይ መሥራት ስለምትፈልግ በዚህ ዙሪያ ተሰማርታ ለሀገሯና ለሕዝቧ አንድ ትልቅ አበርክቶ ማኖር እንደምትፈልግ ገልፃለች።

"የእኔ ትልቁ አቅምና ለዚህ ስኬት ያበቃኝ የጊዜ አጠቃቀሜ ጥሩ ነው"፣ የምትለው ሃናን፤ በተለያዩ ነገሮች ጊዜ ከማባከን ይልቅ ሙሉ ሰዓቷን ለትምህርትና ለትምህርቷ ብቻ መዋሏ እንደሆነ ገልፃ፤ ከትምህርቷ ውጪ ለሌላ ነገር ጊዜ እንዳልነበራት ነው የተናገረችው:: ይህ ሁሉ ልፋት በመጨረሻ በስኬት በመጠናቀቁ ደስተኛ መሆኗን ገልፃለች።

ሃናን ስለፈተናውም እንደገለጸችልን፤ ፈተናው



ኖላዊ ጌትዬ፤

ከሌላው ዓመት የተለየና ከባድ ነው የሚባል አይደለም:: ጥሩ ዝግጅት ከተደረገ መሥራት ይቻላል:: በፈተናው ስለተመዘገበው ውጤትም አብዛኛው ተማሪ ለፈተናው የሚመጥን ዝግጅት አድርጓል የሚል እምነት የላትም:: እርስዋ እንዳለችው፤ ፈተና ሲቃረብ ብቻ ሳይሆን ከታች ጀምሮ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል:: "ፈተና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ነው የተሰጠው:: በዚህ ምክንያት ኩረጃ የለም:: ሁሉም የራሱን ነው የሠራው:: ይህ ለተገኘው ዝቅተኛ ውጤት ምክንያት ይሆናል የምል ግምት አለኝ" ስትልም ገልጻለች::

ከእርስዋ በኋላ ላሉ ተማሪዎችም በሰጠችው ምክር ጊዜያቸውን ላልተገባ ነገር ከማዋል ተቆጥበው በትምህርታቸው ላይ ትኩረት በማድረግ ለውጤት ለመብቃት መዘጋጀት ይኖርባቸዋል:: በኋላ ላይ ለቁጭት እንደሚዳረጉ ከወዲሁ ሊረዱ ይገባቸዋል:: በጥረት የሚገኝ ውጤት ደስታን እንደሚሰጥ ከእርስዋ ውጤት እንዲማሩም ምክሯን ለግሳለች::

ሃናን ለውጤቷ ማማር የቤተሰቦችዋ እገዛም ከፍተኛ መሆኑን ተናግራለች:: ቤተሰቦቿ በሚያስፈልጋት ነገር ሁሉ ከጎኗ ሆነው ሲያግዟት እንደነበር የምትናገረው ሃናን፤ ለፈተናው በአዕምሮ ዝግጁ እንድትሆን፣ እንዳትፈራ፣ እንዳትጨናነቅ በማድረግ የምትፈልገውን ነገር በማመቻቸት እንዳገዟት ገልጻለች:: ላደረጉላት ድጋፍም ቤተሰቦችዋን አመስግናለች::

ሁሉም ሰው ዓላማና ግብ ካለው ውጤታማ መሆን ይችላል የምትለው ሃናን፣ ማንኛውም ሰው ነገ ማሳካትና መድረስ ለሚፈልገው ደረጃ በሚችለው አቅም ተግቶ መሥራት እንዳለበት ገልጻለች::

ሌላው በትምህርት ዘመኑ ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገበው ተማሪ ኖላዊ ጌትዬ ይባላል:: ኖላዊ በተፈጥሮ ሳይንስ የትምህርት ዘርፍ 617 ነጥብ በማስመዝገብ ከፍተኛ ውጤት ካስመዘገቡ ተማሪዎች መካከል አንዱ ለመሆን ችሏል:: ኖላዊ ሁሉንም ያስፈተናቸውን ተማሪዎች ማሳለፍ ከቻሉ ጥቂት ትምህርት ቤቶች መካከል አንዱ በሆነው ኮተቤ ዩኒቨርሲቲ ትምህርት ቤት ተማሪ ነው:: ከመጀመሪያው የትምህርት ደረጃዎች ጀምሮ በትምህርቱ ጥሩ ውጤት ካላቸው ጎበዝ ከሚባሉ ተማሪዎች መካከል እንደነበር የሚናገረው ኖላዊ፤ በዘንድሮው ብሔራዊ የዩኒቨርስቲ መግቢያ ፈተና ጥሩ ውጤት ለማምጣት ሙሉ ጊዜውን ትምህርቱ ላይ ብቻ በማድረግ ዝግጅት ሲያደርግ እንደቆየ ይናገራል።

በ2011ዓ.ም የስምንኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና ከፍተኛ ውጤት በማምጣትና የኮተቤ ዩኒቨርስቲ ትምህርት ቤት ያወጣውን የመግቢያ ፈተና በብቃት በማለፍ ትምህርቱን የቀጠለው ኖላዊ፤ ከዛን ጊዜ ጀምሮ ውጤታማ ለመሆን ግብ አስቀምጦ ሲሠራ እንደቆየና የመጨረሻ ውጤቱም መልካም በመሆኑ ደስተኛ እንደሆነ ተነግሯል።

ለፈተናው ዝግጅት ያደረገበት መንገድ ምን ይመስል እንደነበር ኖላዊ እንደነገረን፤ የትምህርት አይነቶች ተመሳሳይነት አላቸው፣ የአስራ አንደኛ ክፍል ከአስራ ሁለተኛ ክፍል ጋር ተዛማጅነት አለው፣ የትምህርት አይነቶቹን አነጣጥሎ ከማንበብ ይልቅ የሁለቱንም የትምህርት አይነቶች መጽሐፍት ጎን ለጎን አስቀምጦ አንድ ኖት/ማስታወሻ እንደሚያወጣና በዚህ መሠረት የያዘውን ማስታወሻ በማጥናት ነበር የሚጠቀመው:: እንዲህ ያለው የጥናት ዘዴ ጊዜውን በአግባቡ ተጠቅሞ ውጤታማ መሆን አግዞታል።

የትምህርት ቤቱ ማኅበረሰብ በአጠቃላይ በተለይ ደግሞ መምህራኖቻችን ይህንን የመሰለ ውጤት እንድናመጣ ለፍተዋል የሚለው ኖላዊ፤ የተለያዩ የማትሪክ ጥያቄዎችን በመስጠት፣ የተማርናቸውን ትምህርቶች በመከለስ ለፈተናው ብቁ እንዲሆኑ መምህራኖቻቸው ከፍተኛ ጥረት እንዳደረጉ ይገልፃል።

ቤተሰቦቹም የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ በማቅረብ ድጋፍ ሲያደርጉለት እንደቆዩ የሚናገረው ኖላዊ፣ በተረጋጋ መልኩ መጨናነቅ ሳይኖር ትምህርቱን ማጥናት እንዲችል እገዛ ሲያደርጉለት እንደነበር ይናገራል። በመጣው ውጤት ደስተኛ እንደሆነ የሚናገረው ኖላዊ ውጤቱ ግን ከዚህ በላይ ቢያንስ እስከ 625 ድረስ ከፍ ይላል ብሎ ጠብቆ እንደነበር ነገር ግን አሁን በተገኘው ውጤት እንዳልተከፋ ተናግሯል።

የአብዛኛው ተማሪ ውጤት ዝቅ የማለቱ ምክንያት ‹‹አብዛኞቹ ተማሪዎች ትምህርቱን የመሥራት አቅምና ችሎታው እያላቸው ነገር ግን ጊዜያቸውን በአግባቡ አልተጠቀሙም:: በአዕምሮም ዝግጁ ሆነው አይደለም ለፈተና የተቀመጡት:: ይህ መሆኑም በመጣው ውጤት ላይ ትልቅ ክፍተት ፈጥሯል›› በማለትም አስተያየት ሰጥቷል::

ለፈተና ወደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ባመሩበት ወቅት ያየው ነገር እንዳሳዘነው የሚናገረው ኖላዊ እንደገለጸው፤ አብዛኛው ተማሪ ዝም ብሎ ገብቶ ግቢ አይቶ ለመምጣት የመጣ በሚመስል መልኩ ግቢ ውስጥ በመጮህ፣ በመሮጥ ነው ጊዜያቸውን ሲያሳልፉ የነበረው:: ብዙ ተማሪዎች ለፈተናው በአግባቡ ስላልተዘጋጁ ተስፋ በመቁረጥ ነው ለፈተና የተቀመጡት ሲል ትዝብቱን ይገልፃል።

በተጨማሪ ተማሪ ኖላዊ ሲናገር፤ ጥሩ ተማሪ ለመሆን፣ የአስተማሪ ጥረት በእጅጉ ያስፈልጋል:: እርሱ እንዳለው ለተማሪዎች ውጤት ዝቅተኛ መሆን ችግሩ የተማሪዎች ብቃት ከማነስ ጋር ብቻ አይያያዝም፤ የመምህራንም የማስተማር ብቃት መፈተሽ ይኖርበታል:: አንዳንድ ተማሪዎች ይህን ጉዳይ እንደሚያነሱም ያስረዳል:: እንዲህ ያለው ሀሳብ ለፈተና ወደ ግቢ ከገቡና ከእርሱ ጋር አብረው ከቆዩ ከሌሎች ትምህርት ቤት ተማሪዎች ጋር ሲጫወቱ የተነሳ እንደሆነም ተናግሯል:: ይህም ዝቅተኛ ውጤት እንዲመዘገብ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ያምናል:: በአጠቃላይ ለውጤት ቀውሱ የተማሪው፣ የመምህራን፣ የትምህርት ከባቢያዊ ሁኔታ የየራሳቸው ድርሻ እንደሚኖራቸው ተናግሯል።

"አንድ ነገር ለማሳካት እራስን ለዛ ነገር መስጠት እና ለሚያጋጥሙ ፈተናዎችን ሳይበገሩ ለማለፍ ቁርጠኛ መሆን ወሳኝ ነው›› የሚለው ኖላዊ፤ ‹‹እንደ እኔ ያሉ ተማሪዎች ጊዜያቸውን በአግባቡ ቢጠቀሙ መልካም ነው" ይላል።

የወደፊት ዕቅዱን እና ምን ማሳካት እንደሚፈልግ ኖላዊ ሲናገር፤ ሶፍትዌር ኢንጅነሪንግ በማጥናት ባለሙያ የመሆኑ ሐሳብ አለው:: ከዚህ ውጪ በተለያየ ዘርፍ ዕውቀት እንዲኖረው ይሻል። ዘርፉ በጣም ሰፊ እንደሆነና ጠቅላላ ዕውቀትም እንደሚፈልግ ይገልፃል። ይህንን ለማሳካትም ትምህርቱን አጠናክሮ እንደሚቀጥል እና በዘርፉ ጥሩ ዕውቀት ይዞ ወደ ሶፍትዌር / ኮምፒውተር ዘርፍ ተቀላቅሎ መሥራት እንደሚፈልግ ገልጿል።

ኢትዮጵያን በሶፍትዌር ልማት የሚያስጠራ እና ከዘርፉ ተጠቃሚ የሚያደርገውን ሥራ በተግባር መሥራት እና ማበርከት እንደሚፈልግ የተናገረው ተማሪ ኖላዊ፤ አሁን ላስመዘገበው ጥሩ ውጤት በመጀመሪያ ለአምላኩ፣ በመቀጠልም ሁለንተናዊ ድጋፍ ላደረጉለት መምህራኖቹ፣ ለትምህርት ቤቱ ማኅበረሰብና በተለይ ደግሞ ለቤተሰቦቹ፣ ለጓደኞቹ ያለውን ምስጋናና አክብሮት ገልጿል።

በ2015 የ12ኛ ብሔራዊ መልቂያ ፈተና ባስመዘገቡት ውጤት ኮከብ መሆን የቻሉት ተማሪ ሃናንና ኖላዊ ለቀጣይ ተማሪዎች መልእክት አስተላልፈዋል:: የተማሪዎቹ መርሕ ጊዜን በአግባቡ መጠቀምና ለትምህርትም ትኩረት መስጠት ለስኬት እንደሚያበቃ ነው:: ተማሪዎቹ አፅንኦት ሰጥተው ያስተላለፉት መልእክትም ተማሪዎች ዋና ሥራቸው ትምህርት መሆኑን ተገንዝበው አልባሌ ቦታ ከመዋል ተቆጥበው ጊዜያቸውን ለትምህርት ማዋል እንዳለባቸው ነው:: ተማሪዎቹ እንዳሉት ቀድሞ ባለመዘጋጀት በሚመጣ ውድቀት ከመቆጨት በየእለቱ አስፈላጊውን ነገር በማድረግ ለውጤታማነት መትጋት ይጠበቃል::

# የምድር በረከት

# ግንባታው እየተጠናቀቀ ያለው የድንጋይ ከሰል ማጠቢያ ፋብሪካ

**ወርቅነሽ ደምሰው**

በኢትዮጵያ በማእድን ዘርፍ እየተከናወኑ ካሉ ተግባሮች አንዱ ለሲሚንቶና ሌሎች ኢንዱስትሪዎች በጥሬ እቃነት የሚያገለግለውንና ከውጭ ሲመጣ የኖረውን የድንጋይ ከሰል በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት የሚደረገው ጥረት ነው:: በዚህም በሀገሪቱ በማህበራት ተደራጅተው የድንጋይ ከሰል እያመረቱ ካሉት ማህበራት በተጨማሪ ኩባንያዎች የድንጋይ ከሰል በማምረትና በማጠብ ሥራው እየገቡ ናቸው::

ከማእድን ሚኒስቴር ያገኘነው መረጃ እንደሚጠቁመው፤ በሀገሪቱ ከውጭ የሚመጣውን የድንጋይ ከሰል በሀገር ውስጥ ምርት ሙሉ ለሙሉ ለመተካት የሚያስችል ሥራ እየተሠራ ነው:: የድንጋይ ከሰል በሀገር ውስጥ ለማምረት ፈቃድ የወሰዱ ትልልቅ ኩባንያዎች ወደ ምርት እንዲገቡ ድጋፍ እየተደረገ ይገኛል:: ሌሎች ኩባንያዎችም ወደ ዘርፉ እንዲገቡ የሚያደርግ ሥራም እየተሠራ ነው::

የማዕድን ሚኒስቴር የኮሙኒኬሽንና የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ አወቀ ተስፋው በቅርቡ እንደገለጹልን፤ ከፌዴራል መንግሥት ስምንት ኩባንያዎች የድንጋይ ከሰል ለማምረት የሚያስችላቸውን ፈቃድ ወስደዋል:: በክልሎችም የድንጋይ ከሰል የማምረት ፈቃድ ወስደው በዘርፉ የተሰማሩ ማህበራትና ኩባንያዎች በርካታ ናቸው::

ከውጭ የሚገባውን የድንጋይ ከሰልን በሀገር ውስጥ የመተካት ሥራው ተጠናክሮ መቀጠሉን አቶ አወቀ ጠቅሰው፣ በ2015 በጀት ዓመት በሀገር ውስጥ ከተመረተው 1 ነጥብ 2 ሚሊዮን ቶን የድንጋይ ከሰል ምርት ማግኘት ተችሏል ብለዋል:: በዚህም ከ 7 ሚሊዮን ዶላር በላይ ማዳን መቻሉን ተናግረዋል:: የ2016 በጀት ዓመት ሁለት ሚሊዮን ቶን የድንጋይ ከሰል በሀገር ውስጥ ለማምረት መታቀዱን ነው የሚናገሩት::

በሌላ በኩል ደግሞ ከደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ክልል ያገኘነው መረጃ እንደሚያመላክተው፤ በክልሉ 15 አነስተኛ ደረጃ አምራቾች እና ሦስት በከፍተኛ ደረጃ አምራቾች በአጠቃላይ 18 አምራቾች በማዕድን ዘርፍ በተለይ በድንጋይ ከሰል ልማት ሥራ ፈቃድ ወስደው ተሰማርተዋል::

ከክልሉ በ2015 በጀት ዓመት 748 ሺ24 ቶን ያህል የድንጋይ ከሰል ለማምረት ታቅዶ፤ 209 ሺ398 ቶን ለማምረት ተችሏል:: ከገቢም አንጻር 30 ሚሊዮን ብር ገቢ ለማስገባት ታቅዶ፤ 29 ነጥብ3 ሚሊዮን ብር ገቢ ማግኘት ተችሏል:: በድንጋይ ከሰል ምርት ብቻ ለ600 ዜጎች የሥራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ፣ ለ525 ዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ እድል ተፈጥሯል::

በክልሉ የዳውሮ ዞን በድንጋይ ከሰል ማምረትና እጥበት ሥራ ከተሰማሩት ከፍተኛ ደረጃ አምራቾች ውስጥ አንዱ የኢቲ ማዕድን ልማት አክሲዮን ማህበር ነው:: አክሲዮን ማህበሩ በድንጋይ ከሰል እጥበት ሥራ ለመሥራት በ2014 ዓ.ም ነው ፈቃድ ወስዶ ወደ ሥራ የገባው::

አክሲዮን ማህበሩ በአሁኑ ወቅት በድንጋይ ከሰል እጥበት ሥራ ለመሥራት የሚያስችለውን ፋብሪካ እየገነባም ይገኛል:: ይህ በዳውሮ ዞን ተርጫ የሚገኝ የድንጋይ ከሰል ማበልፀጊያ ፋብሪካ በመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት በተሰናዳውና በደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ክልል በቅርቡ በተደረገው የሚዲያ ባለሙያዎች ጉብኝት ወቅትም ተጎብኝቷል:: በወቅቱም የፋብሪካው ተወካይ አቶ ወንድሙ ምትኩ ፋብሪካው በዓመት አንድ ሚሊዮን ቶን የድንጋይ ከሰል በማጠብ ለሲሚንቶ ፋብሪካዎች በማቅረብ የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሪ ያድናል ብለዋል::

የድርጅቱ ሥራ ሀገሪቱ ከውጭ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ስታስገባ የኖረችውን የድንጋይ ከሰል ምርት በማስቀረት ሙሉ ለሙሉ በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት የተያዘውን እቅድ ለማሳካት የበኩሉን ሚና እንደሚጫወት አዲስ ዘመን ጋዜጣ በስልክ ያነጋገራቸው እኚሁ የአክሲዮን ማህበሩ ተወካይ አቶ ወንድሙ ምትኩ ገልጸዋል::

**የፋብሪካው ግንባታ ሥራ ከ85 በመቶ በላይ ደርሷል:: ቀሪ ሥራዎች ከውጭ የመጡ ለፋብሪካው አገልግሎት የሚውሉ መሣሪያዎች ተከላ ብቻ ነው**

እሳቸው እንደሚሉት፤ ይህ ኩባንያ በማዕድን ሚኒስቴር በማእድን ዘርፍ ላይ እንዲሠሩ ከተመረጡት ኩባንያዎች መካከል አንዱ ነው:: የኩባንያው ዋና ዓላማ ከውጭ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ተገዝቶ የሚመጣውን የታጠበ ድንጋይ ከሰል ምርት በሀገር ውስጥ ምርት በመተካት ለሲሚንቶና ብረታ ብረት ፋብሪካዎች ማቅረብ ነው::

‹‹የድንጋይ ከሰል የሚያመርት ፋብሪካ ለመገንባት ከመታሰቡ በፊት በዳውሮ አካባቢ ያለውን የድንጋይ ከሰል ክምችት ምን ያህል ነው በሚል አዋጭነቱ በሚገባ በጥናት ተረጋግጧል›› ያሉት ተወካዩ፣ ይህ ታውቆ ወደ ፋብሪካ ግንባታ መገባቱን አስታውቀዋል:: ዞኑ በቂ የድንጋይ ከሰል ማእድን ክምችት እንዳለው ጠቅሰው፣ እኛ ባረጋገጥነው መሠረት በዳውሮ ዞን ያለው የድንጋይ ከሰል ክምችት ሠላሳ ዓመታት ያህል የሚያሠራ ነው ሲሉም አብራርተዋል:: አጎራባች በሆኑት ኮንታና ጎፋ ዞኖችም ላይ ቢያንስ እስከ 60 ዓመታት ያህል የሚያሠራ የድንጋይ ከሰል ክምችት ስለመኖሩ አረጋግጠናል›› ብለዋል::

አቶ ወንድሙ እንዳሉት፤ ፋብሪካው በሰዓት 150 ቶን የድንጋይ ከሰል የሚያመርት ሲሆን፤ በዓመት አንድ ሚሊዮን ቶን የድንጋይ ከሰል ማምረት ይችላል:: ፋብሪካው በሰዓት በሚያጥበው 150 ቶን የድንጋይ ከሰል እንዲሁም በዓመት አንድ ሚሊዮን ቶን የድንጋይ ከሰል የሚያጥብ በመሆኑ በሀገር ውስጥ ካሉት የድንጋይ ከሰል የሚያጥቡ ፋብሪካዎች የተለየ ያደርገዋል:: ከውጭ የሚመጣው 75 በመቶ የሚሆነው የድንጋይ ከሰል ምርትንም ይሸፈናል ተብሎ በመንግሥት አቅጣጫ የተቀመጠበት ፋብሪካ ነው ብለዋል:: ዘመኑ የደረሰበትን ቴክኖሎጂ ደረጃ እንደሚጠቀምም ተናግረዋል::

አሁን ፋብሪካው ስላለበት ደረጃ አቶ ወንድሙ ሲያብራሩ እንዳሉትም፤ የፋብሪካው የፋውንዴሽን ዲዛይን ሥራ ተሠርቶ ተጠናቋል:: የዲዛይኑ ደረጃም በቱርክ ባለሙያዎች እና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጂኦሎጂስቶች ተረጋግጧል:: የፋብሪካው የጥገና ክፍል፣ መጋዘን፣ የውጭ ሀገር ዜጎች የሚያርፉበት (ገስት ሀውስ) ፤ የአስተዳደር ህንጻ እና ለጋራዥ አገልግሎት የሚውል ህንጻ ፣ መኪናዎች ሲወጡና ሲገቡ የሚመዘኑበት የሚዛን ቦታ ፣ የሠራተኞች ማደሪያ ህንጻና ለካፍቴሪያ አገልግሎት የሚውሉ ህንጻዎች ግንባታ ተጠናቅቋል::

የመንገድ ሥራን ጨምሮ በአብዛኛው በሚባል ደረጃ ሥራዎች መጠናቀቃቸውን ጠቅሰው፣ አሁን ላይ የፋብሪካው ግንባታ ሥራ ከ85 በመቶ በላይ መድረሱን አመልክተዋል:: ቀሪ ሥራዎች ከውጭ የመጡ ለፋብሪካው አገልግሎት የሚውሉ መሣሪያዎች ተከላ መሆናቸውንም አብራርተዋል::

እነዚህን ቀሪ ሥራዎች ለመሥራት የሚያስፈልጉት የውጭ ሀገር ሙያተኞች ወደ ሀገር ውስጥ ገብተዋል ያሉት አቶ ወንድሙ፤ በጥቂት ቀናት ውስጥ ፋብሪካው ወደ አለበት ቦታ ላይ መጥተው የመሣሪያዎቹን ተከላ እንደሚያከናወኑም ጠቁመዋል:: የተከላ ሥራው እንደተጠናቀቀም ወደ ሙከራ ማምረት ሥራ እንደሚገባ ተናግረዋል:: ከመጪው ህዳር ወር በኋላ መቶ በመቶ በሚባል ደረጃ ወደ ማጠብ ሥራ ይገባል ሲሉም አስታውቀዋል::

ከሥራ እድል ፈጠራ አንጻር ፋብሪካው አሁን በደረሰበት ደረጃ ቀንና ማታ በፈረቃ እያሠራ ለ410 ቋሚና ጊዜያዊ ሠራተኞች የሥራ እድል መፍጠሩንም አቶ ወንድሙ አስታውቀዋል:: ፋብሪካው ተጠናቅቆ በሙሉ አቅሙ የማምረት ሥራ ሲጀምር ለ 400 የዩኒቨርሲቲ ተመራቂዎች ቋሚ የሥራ እድል እንደሚፈጥር ጠቁመው፤ በጊዜያዊነትም ለበርካታ ዜጎች የሥራ እድል እንደሚፈጥር ይናገራሉ::

የዳውሮ ዞን ለድንጋይ ከሰል ምርት ተመራጭ የሆነበት በርካታ ምክንያቶች እንዳሉም ጠቅሰው፣ አካባቢው ላይ የሚገኘው የድንጋይ ከሰል ክምችት ብቻ ሳይሆን የድንጋይ ከሰሉ ፋብሪካው ከተቋቋመበት አካባቢ በቅርበት ርቀት ላይ የሚገኝ በመሆኑም ነው ይላሉ::

አቶ ወንድሙ የልማቱ ተግዳሮት ያሏቸውንም ጠቅሰዋል:: ከውጭ ሀገር ተገዝተው ወደ ሀገር ውስጥ እየተጓጉዙ ያሉትን ማሽነሪዎች ከወደብ ወደ ዳውሮ ዞን ለማምጣት ከወላይታ ሶዶ እስከ ዳውሮ ዞን ያለው መንገድ ምቹ አለመሆን ችግር እንደሆነባቸው ይጠቅሳሉ::

‹‹ማሽነሪዎችን በተሳቢ መኪናዎች በኮንትራት ስናመጣ በመንገድ ችግር ለመቆም እየተገደዱ ናቸው፤ በዚህ የተነሳም በኩባንያው ላይ በቀን አምስት ሺ ብር ኪሳራ እየደረሰ ነው›› ይላሉ:: አንድ ኮንቴይነር የፋብሪካ እቃ ሲመጣ ከድሬዳዋ ወይም ከአዲስ አበባ ማዕከል 290ሺ ብር ይከፈላል፤ ከዚያ እዚህ እስከሚደርስ ደግሞ ያለው ከፍተኛ የመንገድ መሠረተ ልማት ችግር በአምስትና ስድስት ቀናት መድረስ ያላባቸው መኪናዎች መንገድ ላይ 20 ቀናትና ከዚያ በላይ እንዲቆዩ እያደረገ ነው ሲሉ ያብራራሉ:: ይህ ሁሉ ድርጅቱን ለኪሳራ እየዳረገው መሆኑን ይጠቁማሉ::

ይህ ሁሉ ችግር በፋብሪካው ግንባታ ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ መፍጠሩን ጠቅሰው፣ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ይጠናቀቃል ተብሎ በእቅድ የተያዘውን የፋብሪካውን ሥራ ወደ አንድ ዓመት እንዲጓተት ማድረጉን ይናገራሉ:: ይህ ደግሞ የፋብሪካውን ሥራ ሊያስተጓጉል እንደሚችል ገልጸዋል::

የመብራት ኃይል ማነስ ሌላው ችግር መሆኑንም አቶ ወንድሙ ጠቁመዋል:: ፋብሪካው ያለበት ዳውሮ ተርጫ አካባቢ መሆኑን ጠቅሰው፣ ለአካባቢው ከጊቤ ሁለት የተዘረጋው የመብራት ኃይል በጣም ከፍተኛ ችግር ያለበት በሳምንት ሁለት ጊዜ አልያም ሦስት ጊዜ ብቻ ብቅ የሚል መሆኑን ያመለክታሉ:: ‹‹ የፋብሪካውን ግንባታ አጠናቅቀን ወደ ማምረት ሥራው ስንገባ፣ አሁን ባለው ሁኔታ በጣም ከፍተኛ የኃይል አቅርቦት እጥረት ይገጥመናል›› ሲሉ ስጋታቸውን ይጠቁማሉ:: በዚህ ሁኔታ የራሳችንንም፣ የመንግሥትን እቅድ ለማሳካት እንቸገራለን ሲሉም ይገልጻሉ:: የሃይል አቅርቦቱ ከጊቤ ሦስት የሚገኝ ከሆነ የተቀመጠውን እቅድ ለማሳካት ፋብሪካውን የሚያግደው እንደሌለም ተናግረዋል::

እሳቸው እንዳሉት ፤ የድንጋይ ከሰል ማምረቱ ሥራ ከገበያ አንጻር ምንም ችግር አይኖርም:: የድንጋይ ከሰል ፍላጎትና አቅርቦቱ በንጽጽር የሚቀርብ አይደለም:: ፍላጎቱ በጣም ከፍተኛ ነው፤ አቅርቦቱ በጣም ዝቅተኛ ነው:: የአቅርቦቱን መጠን ለማመጣጠን ይህ ፋብሪካ ወሳኝ ሚና ይጫወታል:: የሲሚንቶ ዋጋ ንረትን ለማረጋጋትም የድንጋይ ከሰል በሀገር ውስጥ መመረቱ የራሱ አስተዋጽኦ ይኖረዋል::

‹‹በያዝነው እቅድ መሠረት በ2016 ዓ.ም እስከ ጥቅምት ወር መጨረሻ ድረስ ግንባታውን እንጨርሳለን ብለን ነበር›› ያሉት አቶ ወንድሙ፤ ፋብሪካው ያለበት አካባቢ ሙቀታማ መሆኑም ሌላው ተግዳሮት መሆኑን ጠቅሰዋል:: ከውጭ ሀገር የመጡት ባለሙያዎች ከሙቀቱ ጋር ተያይዞ በህዳር ወር( ከህዳር 15 እስከ 30 ባለው ጊዜ) ውስጥ ሠርተን እናስረክባል የሚል ሃሳብ እያቀረቡ እንደሆነም ተናግረዋል::

ድርጅቱ በአክሲዮን የተቋቋመና በሀገር ውስጥ ባለሀብቶች የተመሠረተ መሆኑን ጠቅሰው፣ እንደ ሀገር የድንጋይ ከሰል ምርት በሀገር ውስጥ ለማምረት የተያዘውን እቅድ ለማሳካት እየሠራ መሆኑን አስታውቀዋል::

ከውጭ ይመጣ የነበረውን የድንጋይ ከሰል ምርት በሀገር ውስጥ ምርት የመተካቱ ሥራ በራሱ ለሀገሪቱ ትልቅ እምርታ መሆኑን አቶ ወንድሙ ጠቅሰው፣ የማዕድን ሀብትን በማስተዋወቅ በሀገር ውስጥ ያለውን እምቅ አቅም አጎልቶ በማሳየት በኩል የሚዲያ ተቋማት ትልቅ ድርሻ መውጣት እንዳለባቸውም አስገንዝበዋል::

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## እሳት እና ውሀ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ባሏ ትቷት የኮበለለው ጎረቤቴ ቡና ስትወቅጥ ይሰማኛል.. ብቻዋን ልትጠጣው:: ጽናቷ እንዲህ ተክዤ ባለሁበት ሰዓት መበርቻዬ ነው:: ብቻዋን ጀግና የሆነች ሴት ናት:: ትላንት የማያስቆጫት..ነገ የማያስጎመጃት:: አንዳንድ ጊዜ እሷም መሆን እሻለው..ለምንም ለማንም ግድ የሌላትን ነፍሷን::

..........

ያልገቡኝ እንዲገቡኝ ብዙ ጠይቄ፣ ብዙ መጽሀፍትን አገላብጨ አውቃለው:: ግን አሁንም እንዳልገባኝ ነኝ:: በገባ ጥያቄ ያልገባን ሕይወት መኖር..መምረር..ነው አልኩ:: ከመምሬ አድባር ስር ጌታዋን ጥበቃ ቁጭ እንዳለችው ነፍስ፣ በኤፍራታዱር ጌታን እንዳስተኛችው ግርግም ነፍሴ ማረፊያ ቢኖራት:: ልቤ ቦታ ቢያገኝ..እላለው

ሕይወት..መንታ ነፍስ ናት:: እየሳቁና እየተሳቀቁ መጥተው የሚሄዱባት..ኖረው የሚያልፉባት:: የእግሬን መረማመጃ ከምን ባንጸው ከእንቅፋት እንደምድን አስቤ አልደረስኩበትም:: የሆነ ነገር እሻለው..እኔም ያልገባኝን የሆነ ነገር:: ለሀሳቤ ዓለም ጠባኛለች:: ዞሬ እዛው ነኝ::

የዓለም መጥበብ የሀሳብ መጥበብ እንደሆነ አልገባኝም:: ሰው በሀሳቡ ሲጠብ ዓለምን በጋቱ ይሰነዝራታል:: ዘላለማትን እንደ አንድ ቀን ንጋት ይዳፈራል:: አእምሮ ከፍትህ ሲርቅ፣ ልብ ፍቅርን ሲያጎድል ጠይቀን ለማንመልሰው ብንመልሰውም ልክ ለማንሆነው ግብዝ እውቀት እየተሰናዳን ነው::

ሁለት አይነት ሰዎች አሉ..በመኖር የሚስቁና የሚሳቀቁ:: ለሁለቱም ሕይወት አንድ አይነት ናት:: መነሻዋን የፈጣሪ ሀሳብ አድርጋ መድረሻዋን ሞትና ትንሳኤ ያደረገች:: ትንሳኤዋን ረስተው ሞቷን ብቻ የሚያስታውሱ ይሳቀቁባታል:: ሞቷን ረስተው በትንሳኤዋ ውስጥ የቆሙ ደግሞ ለመሳቀቅ ጊዜ አያገኙም:: እናም..ልብሳችንን ከፍ አድርገን ዓለምን የምናይበትን መነጽራችንን እናብስ..ያኔ ልክ መሆን እንጀምራለን:: የሚል ሀሳብ ከገባኝ ዘመን የለውም:: ፍርሀት የአእምሮ መጋረጃ ነው:: ጥሩውን እንዳንመርጥ የሚያደርግ:: ፍርሀት የስጋት ቦታ ነው:: የጥርጣሬና የተስፋቢስነት መነሻ:: ፍርሀትን ማሸነፍ ዓለምን መረዳት ነው:: የፍርሀት ማብቂያ የሕይወት መጀመሪያ ነው:: ፍርሀታችን የተሸነፈበት ቦታ ጋ መኖር እንጀምራለን:: እሱጋ ሕይወት አለ:: የሕይወት ትላልቅ ጥያቄዎች ከፈራ አእምሮና ልብ የሚወጡ ናቸው:: የሚል እውቀት ካወኩ ሰንብቻለው:: ግን አልበረታሁም:: ላለመፍራት ብዙ ታገልኩ:: የባሰ ፈሪ ሆንኩ..

..........

እንደ ጎረቤቴ ግድ የሌለው አእምሮ ናፈቀኝ:: ለሆነውና ለሚሆነው ግድ የሌለው:: ስለነገ የማይጨንቀው..ስለዛሬ ምንም የማይመስለው:: ሕይወትን በግዴለሽነት ውስጥ አላውቃትም:: ስኖር ተጠንቅቄና ተሳቅቄ ነው:: ግን እንደሀሳቤ ሩቅ አልተራመድኩም:: ከዛሬ የሚያርቀኝን እውነት እሻለው::

መኖር ስሻ ትቼው ወደመጣሁት ውብ ጊዜዬ አቀናለሁ:: በዛ ጊዜ ሕይወትን ያጣመችልኝ አንድ ነፍስ አለች:: ከእናቴ ቀጥሎ ሁሌ አነሳታለሁ:: አሁን በሕይወቴ ውስጥ ሁለቱም የሉም:: የእናቴ ትከሻ እንደ ገነት አውድ ናቸው...ብርሀን እየረጩ ውጋግ የሚሰጡኝ:: ያቀፉኝ ክንዶቿ..የጨበጡኝ እጆቿ በገነት እርፍኝ ደጅ እንኳን ደህና መጡ ሲሉ ድቃንን እንደሚቀበሉ መላዕክተ ሀመልማል መሳይ:: ያስተኛኝ ደረቷ..ያሞቀኝ ጉያዋ እንደ ክረምት ጣይ በነፍስ ቆፈን ላይ የሚያርፍ..:: በዚች ሴት ትከሻ ላይ ሕይወት ጥማኝ ሰው ሆንኩ:: ከዛም ከአንዲት የእናቴን መሳይ ነፍስ ካላት ወጣት ጋር ተዋሃድኩ:: የእናትና የሚስት ፍቅር ለወንድ ልጅ የዘላለም ድርሰቱ ነው..በእውነተኛ ታሪክ ላይ ተመስርቶ የሚጽፈው:: ሰው የሕይወትን ጨምዳዳ እንዳያይ አይኑን ቢሸፍን ኖሮ ብዙ ደስታ እንዳለው ይቆጥር ነበር:: ከእናት ወደ ሚስት ከሚስት ወደ ልጅ ከዛም ወደልጅ ልጅ..ሕይወትን በዚህ ብቻ እናሞካሻት ነበር::

የሕይወት ትልቁ ተንኮሏ ድንገት ሰጥታ ድንገት መንሳቷ ነው:: ከእናት እና ከሚስቴ በኋላ ሕይወትን አላምናትም:: በሁለቱም በኩል የዓለምን ክፋት አልተማርኩም:: በሁለቱም በኩል ስለሕይወት አልሰማሁም:: ሕይወት ውብ ብቻ እንደሆነች ነው የተማርኩት:: የእናት ልብ የልጆቿ የመከራ መሸፈኛ ነው:: የእናት ልብ ለልጅ እንደኳዳ ነው..ገመና መሸፈኛ:: በወላጆቻችን የተሸፈነ ብዙ ገመና እንዳለን የሚገባን ወላጅ ከሆንን በኋላ ነው:: በእናት ጥላ ስር የብዙ ልጆች መከራ ተከልሏል::

አንድ ልጅ አለችኝ..ከዛች ሴት የወለድኳት:: ማንነት ውርስ አይደል? ልክ እንደ እናቴና ሚስቴ ልጄንም ክፉ ላሳያት አልቻልኩም:: መከራዎቼን ደብቄ..ሳቄን እያሳየኋት አባቷ ነኝ:: ጉንጭዋን ስሜ አጠገቧ አረፍ አልኩ:: ብቻዋን ስትሆን በምትዝናናበት ዘመን አመጣሽ ቲክ ቶክ እየተዝናናች አቀርቅራለች::

‹አባ ባለፈው በለቀኩት ፎቶ እኮ ከሁለት መቶ በላይ አስተያየት አገኘሁ:: ደስ አይልም? አለችኝ በበራ ፊት.. አይኗን ከስልኳ ስክሪን ላይ ሳትነቅል::

ዝም አልኳት:: ብዙ ጊዜ እንዲህ አውርታኝ ታውቃለች:: አብሬአት ስሆን ብዙ ጊዜአችን የሚያልፈው በፎቶ ነው:: እንዲ ሁን እንደዛ ሁን እያለችኝ::

‹ትላንትና ለፖስትኩት ፎቶ የተሰጠኝን አስተያየት ላንብብልህ› ብላ..በተቀመጠችበት ተመቻቸች:: ዝም ብዬ አስተውላታለሁ:: ዘመን ሰው ይፈጥራል ይገላልም የሚለው አባባል የመጣልኝ እሷ ፊት ነው:: ዘመንን በስልት ካልተቀበሉት ስለት ነው:: ዘመንን በጥበብ ካልተዋሃዱት ጥበት ነው:: ጊዜን በእውቀት ካልሄዱበት ድቀት ነው እያልኩ ስብሰለሰል ወሬዋ አደናቀፈኝ::

ልጄ ስታወራ ጣልቃ የማይገባ አባት ነበርኩ:: ያሰኛትን እንድትሆን የበዛ ነጻነት ሰጥቻት ነበር:: ግን ይሄ ሁሉ ልክ እንዳይደለ የገባኝ ዘግይቶ ነው:: ነጻነት በአግባቡ ካልተጠቀሙበት ቀጣፊ ነው:: ብዙ ነፍሶች የተቀጠፉት በበዛ ነጻነታቸው ነው:: እናም ልጄን እንዲህ አልኳት..

‹በልቤ ውስጥ ዘመን ያላደበዘዛቸው ሁለት ሴቶች አሉ... እናቴና እናትሽ:: አያትሽ እና ሚስቴ:: እንደነዚህ ነፍሶች በአባትሽ እና በባልሽ ልብ ውስጥ መቼም እንዳትረሺ የሕይወት ሕግን እሰጥሻለው:: የመጀመሪያው..እንደእናት አስቢ:: ቀጥሎ እንደ ሚስት በመጨረሻም እንደ ልጅ::

ዝም ብላ ስታደምጠኝ አያታለሁ:: የከፈተችው ቪዲዮ ድምጽ አውጥቶ ሲረብሸን ዘጋችው::

‹እንደ እናት ማሰብ..ሴት ብቻ አለመሆን ነው:: በአእምሮና ልብ መንገስ:: የአንቺ ለሆነው ሁሉ ክብርና ዋጋ መስጠት:: እንደ ሚስት ማሰብ በፍቅር የበረታ ክንድን መፍጠር ነው:: በአንቺ በኩል ወደምድር የሚመጡ ነፍሶች እንዳሉ በማሰብ ከሁሉም ትልቁ ፍቅር በርሽን መክፈት:: እንደ ልጅ ማሰብ ብዙ ነገዎች እንዳሉሽ ተረድተሽ አካሄድሽን ማስተካከል ነው::

‹አሁን ያለችው ኑሃሚን ደስታ አልሰጠችህም? ከልጄ የተነሳ ጥያቄ ነበር::

‹በጣም ስለምወዳት እንድትጎዳብኝ አልፈልግም:: እናም እናትሽና እናቴ በሄዱበት የሴትነት ጎዳና ላይ እንድትራመጂ እሻለው› ክንዴን እያሳየኋት ‹ይሄ ክንድ መቼም አይጥልሽም.. እስከፈለግሽው ድረስ አብሮሽ ነው::

‹በጣም ቀላል ከሆነና ሁሉም ሊያደርገው ከሚችል ነገር ራስሽን መከልከል አለብሽ:: በጣም ከባድ ከሆነና ሁሉም ሰው ሊያደርገው ለማይችል ነገር ልብሽን ስጪ›

‹ያ ነገር ምንድነው?

‹የመጀመሪያው ዋጋ ያላት ሴት መሆን ነው:: ሁለተኛው ዋጋ ያላት ሴት ሊያደርጉሽ በሚችሉ ነገሮች ላይ መጠመድ ነው:: ሶስተኛው..አራተኛው..አምስተኛው..ራስሽን መሆን ነው› አልኳት::

‹የአንተ ልጅ ሆኜ ዋጋ የሌላት ሴት የምሆን ይመስልሀል?

‹እሱ ዋስትና አይሆንሽም:: የማንም ልጅ ብትሆኚ አካሄድሽን ካላስተካከልሽ መውደቅሽ አይቀርም:: እንዳትወድቂ ደግሞ የማይጥል ሀሳብና እምነት ያስፈልግሻል:: የማይጥል ሀሳብና እምነት ደግሞ ከቀላል ሳይሆን ከከባድ ተግዳሮት ውስጥ የሚገኙ ናቸው:: ጊዜሽን ተጠቀሚ..ጊዜ ወዳሻሽ ለመሄድ መረማመጃሽ ነው::

‹ከየት ልጀምር?

‹የማይቻል ከሚመስለው› መለስኩላት::

ጣቷን ከንፈሯ ላይ ጥላ ‹የማይቻል የሚመስል..የማይቻል የሚመስል? አለች::

‹አሁን አንቺ እያደረግሽው ያለው ነገር ሁሉም የሚችለው ቀላል ነገር ነው::

‹ምንድነው እሱ?

‹ድረሺበት› አልኳት:: ሳቅ ብላ ዝም አለች:: የገባት ይመስላል..

‹የሕይወት መብቀያ ልብ ነው:: ሕይወት ያለው ልብ ውስጥ ነው:: የልብሽና የአእምሮሽ ሴት ሁኚ›

‹የልብና የአእምሮ ሴት መሆን ምን አይነት ነው? ስትል ጠየቀችኝ::

‹ሕይወት ሲገባሽ ይገባሻል› መለስኩላት::

‹ሕይወት አልገባኝም?

‹ሕይወት ከጊዜ ነው የሚጀምረው› ብዬ ዝም አልኩኝ:: ድጋሚ እንዳትጠይቀኝ በሚመስል ሁናቴ የፊቴን አቅጣጫ ወደሌላ አዞሬ ተቀመጥኩ:: ዳርዳርታዬ ቢገባት ምኞቴ ነው:: ብዙ ልናገራት አቅም ነበረኝ ግን በአንዴ ሳይሆን ቀስ በቀስ ልሰራት አምኜ ዝግታን መረጥኩ::

አሁን ላለችው ልጄ ሕይወት ማለት ደስታ ብቻ ነው:: ማሕበራዊ ሚዲያ ላይ ተጥዳ ሙገሳና አድናቆት ማግኘት ብቻ ነው:: በለበሰችው ልብስና በተጫማችው ጫማ ተከታይ ማፍራት ነው:: ባልተገቡ ፎቶዎች ኮሜንት መሰብሰብ ነው:: አሁን ላለችው ልጄ ሕይወት ማለት ጊዜ እንደሆነ አልገባትም::

.........

ወደራሴ ዞርኩ..ወደፍቅር አልባው ራሴ::

ፍቅርን ከልቤ ጽላት ላይ ፍቄዋለው:: መኖር በታከተው፣ ፍቅር በሌለው ልብ ውስጥ ነኝ:: ወደነገ የሚያራምድ አቅምን መጣያ ከዘራ እሻለው:: የሕይወት ትልቁ ባዶነት የኔ ከሚሉት ሰው እቅፍ ውስጥ መራቅ ነው:: ወደተውኩት እቅፍ መመለስን ምርጫ አደረኩ:: ፍቅር ባለበት ሕይወት ውስጥ መኖር ጥያቄ ፈጥሮ አያውቅም:: የጥያቄዎቻችን መጀመሪያ የሕይወት ትርጉም አልባ መምሰል ነው:: እናም እንጠይቃለን..ምንድነኝ..ምንድነን? ስንል::

መጨረሻችን በመጀመሪያችን ውስጥ ነው ያለው:: የነገ ኮቴዎች ከአሁን የሚጀምሩ ናቸው:: እናቴን አይነትና ሚስቴን መሳይ ሴት ከጀልኩ...ባሏ ትቷት ወደኮበለለው ጎረቤቴ ሸፈትኩ::

ከክንዷ ሳርፍ፣ ከጉያዋ ስገባ..መኖርና ሕይወት ይጥሙኝ ይሆናል:: እድሜና ሰው መሆን አልጠገብ ይሉኝ ይሆናል:: ብቻ ከእሷ ልኑር..

# ዓለም አቀፍ

## አሜሪካ ከእስራኤል ጎን እንደምትቆም አስታወቀች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የአሜሪካው የውጭ ጉዳይ ኃላፊ አንቶኒ ብሊንከን እስራኤል በሐማስ ለተፈጸመባት ጥቃት በጋዛ ላይ የአጸፋ እርምጃ እየወሰደች ባለበት ጊዜ አሜሪካ ለእስራኤል ያላትን አጋርነት ለመግለጽ በእስራኤል ጉብኝት እያደረጉ ነው።

ብሊንከን ከእስራኤሉ ፕሬዚዳንት አይዛክ ሄርዞግ እና ከጠቅላይ ሚኒስትር ቤንያሚን ኔታኒያሁ ጋር ተገናኝተው ተነጋግረዋል።

ብሊንከን ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር በመሆን በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫም፤ አሜሪካ በየትኛውም ጊዜ ከእስራኤል ጎን እንደምትቆምና ድጋፏን እንደምትሰጥ ገልጸዋል።

ለጉብኝት እስራኤል የገቡት የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ኃላፊ አንቶኒ ብሊንከን ሀገራቸው "በየትኛውም ጊዜ እስራኤልን ለመርዳት" ከጎኗ እንደምትቆም በመግለጽ፤ ለሰላማዊ ሰዎች ጥበቃ ማድረግ አስፈላጊ ነው ብለዋል።

የእስራኤሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ቤንያሚን ኔታኒያሁ ሐማስ "አይሲስ ለአይሲስ በተስተናገደበት መንገድ ምላሽ ያገኛል" ብለዋል።

የእስራኤል ሠራዊት ጋዛ ሰርጥ ውስጥ የማስጠንቀቂያ ወረቀቶችን በመበተን ነዋሪዎች ሐማስ የሚጠቀምባቸው ሕንፃዎችን ስለሚያጠቃ ነዋሪዎች ወደ መጠለያ እንዲሄዱ አሳስቧል።

ስድስተኛ ቀኑን በያዘው እስራኤል በጋዛ ላይ በምትፈጽመው የአየር ጥቃት ቢያንስ 1,417 ሰዎች ሲገደሉ፣ 6,268 ሰዎች ላይ ደግሞ ጉዳት መድረሱን የጋዛ የጤና ባለሥልጣናት ገልጸዋል።

በሌላ በኩል የሐማስ ታጣቂዎች የገደሏቸው እስራኤላውያን ቁጥርም 1,300 ደርሷል። ሌሎች በርካቶች ደግሞ የመቁሰል ጉዳት እንደደረሰባቸው የእስራኤል ባለሥልጣናት አስታውቀዋል።

ብሪቲሽ ኤርዌይስ በእስራኤል ባለው ወቅታዊ ሁኔታ ምክንያት ወደዚያው የሚያደርጋቸውን በረራዎች ለሚቀጥሉት ሦስት ሳምንታት እንዲቋረጡ ወስኗል።

የዩናይትድ ኪንግደም መንግሥት ከእስራኤል ለቀው ለመውጣት ለሚፈልጉ ዜጎቹ የአየር ጉዞዎችን ማመቻቸቱንም አስታወቀ።

## ትዕግሥት አሰፋ እና ጉዳፍ ፀጋይ ለዓመቱ ምርጥ የዓለም ሴት አትሌት ሽልማት ታጩ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያውያኑ አትሌቶች ትዕግሥት አሰፋ እና ጉዳይ ፀጋይን ጨምሮ ሦስት አፍሪካውያን አትሌቶች የዓለም አትሌቲክስ በየዓመቱ ለሚያዘጋጀው የዓለም ምርጥ ሴት አትሌት ሽልማት ታጩ።

ከሁለቱ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በተጨማሪ ኬንያዊቷ ፌይዝ ኪፕየጎን በዘንድሮው የዓመቱ የሴቶች የዓለም ምርጥ አትሌት ዕጩ ውስጥ ተካታለች።

በአጠቃላይ ለሽልማቱ በዚህ ዓመት አስደናቂ ብቃትን ያሳዩ 11 አትሌቶች ዕጩ ሆነዋል።

ኢትዮጵያዊቷ አትሌት ትዕግሥት አሰፋ ባለፈው መስከረም ወር አጋማሽ ላይ በጀርመኗ በርሊን በተካሄደው 48ኛው የማራቶን ውድድር ክብረ ወሰኑን ከሁለት ደቂቃ በላይ በማሻሻል አሸናፊ ሆናለች።

የበርሊን ማራቶን አሸናፊዋ ትዕግስት በርካቶችን ባስደነቀ መልኩ ነበር ሁለት ሰዓት ከ11 ደቂቃ ከ53 ሰከንድ በመግባት የሴቶች ማራቶን ክብረ ወሰን መጨበጥ የቻለችው።

ጉዳፍ ፀጋይም ባለበት የአውሮፓውያን ዓመት መስከረም ላይ በአሜሪካዋ ኦሪገን፣ ዩጂን በተካሄደው የዳይመንድ ሊግ የ5 ሺህ ሜትር ውድድር የዓለም ክብረ ወሰንን በማሻሻል አሸናፊ ሆናለች።

የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና የ10 ሺህ ሜትር አሸናፊዋ ጉዳፍ ውድድሩን 14 ደቂቃ ከ00.21 በመጨረስ እንዲሁም የውድድሩን ክብረ ወሰን በ5 ሰከንዶች በማሻሻል ድንቅ ብቃትም አሳይታለች ተብሏል።

ጉዳፍ ያሻሻለችው ክብረ ወሰን በዘንድሮው ለምርጥ አትሌትነት ዝርዝር ውስጥ በተካተተችው ፌዝ ኪፕየጎን ተይዞ ነበር።

ዜግነቷን ቀይራ ለባህሬን የምትወዳደረው ትውልደ ኬንያዊቷ ዊንፍሬድ ያቪ እንዲሁ በዕጩዎቹ ዝርዝር ውስጥ ተካታለች።

ከደጋፊዎች እና ከዓለም አትሌቲክስ ባለሥልጣናት የተሰጡ ድምጾችም ተሰብስበው አሸናፊዎቹ በአውሮፓውያኑ ታኅሣሥ 11ቀን 2023 ይፋ ይሆናሉ ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

# ነፃ ሃሳብ

## ለጤናማ ኑሮ - ጤናማ አዕምሮ

**መክሊት ወንድወሰን**

ሰዎች የተለያዩ የሰውነት ክፍሎቻቸውን የሕመም ስሜት ሲሰማቸው ወደ ዘመናዊ ሆነ ወደ ባህላዊ ተቋማት በመሄድ መድሀኒት ነው የሚባሉትን በመውሰድ ወደ ቀድሞ ጤናቸው ለመመለስ ይሰራሉ:: ይህን በራሳቸው ማድረግ የሚችሉት አእምሮ ጤናማ ሲሆን ነው፤ ሲታመምስ? ::

የአዕምሮ ጤናን እንደ አዕምሮ ህመም በቀላሉ ትርጓሜ ለመስጠት አስቸጋሪ እንደሆነ፤ ጤነኛ አእምሮ ማለት የአዕምሮ ሕመም ተቃራኒ ማለት እንዳልሆነ የዘርፉ ባለሙያዎች ይናገራሉ:: በአዕምሮ ጤንነት ውስጥ የአዕምሮ ጤነኛ መሆን አንዱ መስፈርት ቢሆንም፤ በሱ የሚያበቃ አይደለም። ከዚህም ከፍ ባለ መልኩ፤ በሕይወት ደስተኛ መሆን፤ እያንዳንዱም ሰው ያለውን እምቅ አቅም አውጥቶ መጠቀምን የሚያካትት እንደሆ ይታማናል::

የአዕምሮ ሕመምን ከሌሎች ሕመሞች ለየት የሚያደርገው በዋናነት፣ በሕመሙ የሚጠቁ ሰዎች ሕመም እንዳለባቸውና እንደ ሌለባቸው የሚያገናዝቡበት፤ ሕመሙ የሚያስከትለውን ጉዳት የሚረዱበት የሰውነት ክፍል ራሱ መታመሙ ነው::

በዚህ ምክንያት በማሕበረሰባችን ውስጥ ሰዎች የአዕምሮ ሕመም ሲከሰት ሕመም የተከሰተ አድርጎ ያለመረዳት፤ በሕመም መያዛቸውን ያለማወቅ፤ ሕመሙ የሚያስከትለውን ተፅንኦ ያለመረዳት ሁኔታ ይስተዋላል::

የሚያስቡበት፤ የተለያዩ ስሜቶች እንዲሰሟቸው፤ የተለያዩ ፀባዮችን የሚመራው ዋናው የሰውነት ክፍል በሕመሙ መጠቃቱ ከሌሎች ሕመሞች የአዕምሮ ሕመምን በብዙ ይለየዋል:: የአዕምሮ ሕመም ለመከሰቱ ስነ-ህይወታዊ፣ ስነ-ልቦናዊና ማሕበራዊ ምክንያቶች ያሉት ሲሆን፤ ሕክምናውም በነዚህ ዘርፎች የተከፋፈለ ነው::

በሽታው ዓለም አቀፍ ደረጃ ስጋት መሆን ከጀመረ ዓመታት እየተቆጠሩ ናቸው። መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በዓለም አቀፍ ደረጃ ከአራት ሰዎች አንዳቸው በምድር ቆይታቸው የአእምሮ ህመም ይከሰትባቸዋል::

በሀገራችን ደግሞ 25 በመቶ የሚሆነው የሕብረተሰቡ ክፍል በእድሜ ቆይታው የአእምሮ የጤና እክል ያጋጥመዋል:: በዚህ ቁጥር ውስጥም አንዳንዶቹ ችግሮች እንደ አእምሮ ጤና ችግር ስለማይታዩ ከጥቂቶች ውጭ ብዙ ሰዎች እንብዛም ለአእምሮ ሕክምና ወደ ጤና ተቋማት አይሄዱም::

ሕሙማኑ ወደ ጤና ተቋማት የሚሄዱት የተለያዩ ሃይማኖታዊ እና ባሕላዊ የሕክምና አማራጮችን ሞክረው ተስፋ ሲቆርጡ በመሆኑ፤ ወደ ጤና ተቋማት የሚሄዱት በከፍተኛ ሁኔታ ከተጎዱ በኋላ ነው:: በተለይም የሕፃናት እና የአፍላ ወጣቶች የአእምሮ ሕመም ከተፈጠሮአዊ የእድሜ ባህሪ ጋር በማዛመድ/በማመሳሰል ወይም ችግሮችን ቀለል አድርጎ በማየት የአእምሮ ጤና ችግሩ ስር እንዲሰድ ያደርጋል::

ለምሳሌ፣ ያክል እንደ አእምሮ ጤና ችግር ከማይቆጠሩት መካከል የተለያዩ ማሕበራዊ ሚዲያዎችን አብዝቶ መጠቀም ወይም ሱስ በሚባል ደረጃ ሲደርስ መመልከት፣ ልጆችን በጭምትነት፣ በረባሽነት እና ሌሎችም መሰል ባህሪያቶች መፈረጅ ለችግሩ እንደ ምክንያት ይቆጠራሉ::

በችግሩ ዙሪያ የተሻለ ግንዛቤ ለማስጨበጥና የአእምሮ ሕክምና አገልግሎት ለማስፋት (ለማህበረሰቡ ተደራሽ ማድረግ) በዓለም አቀፍ ደረጃ በየዓመቱ መስከረም 29 ወይም እ.ኤ.አ October 10 የአእምሮ ጤና ቀን ተከብሮ ይውላል:: ቀኑ በኛም ሀገር ባለፈው ማክሰኞ ተከብሮ ውሏል።

ቀኑ በአእምሮ ጤና ዙሪያ ግንዛቤን ለማስጨበጥ እና መንግስታት፣ የባለድርሻ አካላት እና አጋር ድርጅቶች ለአእምሮ ጤና ተገቢውን ትኩረት እንዲሰጡ ለማድረግ የሚታሰብ ነው:: ይህንኑ ዕለት አስመልክቶም በዓለም በርካታ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ይሰራሉ::

ዘንድሮም በአሉ "ጤና ዓለም አቀፍ ሰብአዊ መብት ነው" በሚል መሪ ቃል ትናንት ተከብሯል፤ መሪ ቃሉ በውስጡ ሶስት መሰረታዊ የሰብአዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደረገ ነው::

1ኛ፣ የአእምሮ ጤና አገልግሎት ማግኘት ሰብአዊ መብት መሆኑ፤

2ኛ. የአእምሮ ሕሙማን አያያዝ ሰብአዊ ክብራቸውን የጠበቀ መሆን እንዳለበት (የአእምሮ ጤና ችግር ያለባቸው የማሕበረሰብ ክፍሎች ከማንኛውም ጥቃት የመጠበቅ መብታቸው እንዲከበር፤

3ኛ የአእምሮ የሕሙማንን የመንቀሳቀስ መብታቸው እንዲጠበቅ፣ ማሕበረሰቡን እና የባለድርሻ አካላትን ግንዛቤ በማሳደግ የአእምሮ ጤና ዓለምአቀፍ የሰብአዊ መብት መሆኑ እውቅና እንዲያገኝ ታስቦ ነው::

በርግጥ በአእምሮ ጤና ችግር ባለባቸው ማሕበረሰብ ክፍሎች ላይ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የሚደርሱ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ብዙ ናቸው:: እነዚህ የመብት ጥሰቶች መቆም የሚችሉት ሁሉም የባለድርሻ አካላት የበኩላቸውን መወጣት ሲችሉ ነው::

የአዕምሮ ሕመም በማንኛውም የእድሜ ክልል ውስጥ ባለ ሰው ላይ ሊከሰት የሚችል ቢሆንም፤ አብዛኞቹ ወይም ከባድና ፅኑ የአዕምሮ ሕመም የምንላቸው ሕመሞች መነሻቸው በወጣትነት እድሜ ክልል ነው:: ይህ እንደ ግለሰብ የሚያስከትለው ተፅንኦ እንዳለ ሆኖ፤ ችግሩ በቤተሰብ፣ ማሕበረሰብ እና በሃገር ላይ ሊያስከትል የሚችለው ተፅንኖ ከፍተኛ ነው::

> **በማሕበረሰባችን ውስጥ የአዕምሮ ህመም ችግሮች የሚያጋጥማቸው አዋቂዎችን ብቻ እንጂ ሕፃናት በአዕምሮ ሕመም የማይጠቁ አድርጎ የመውሰድ የተሳሳተ ግንዛቤ አለ። የአዕምሮ ሕመም ሁሉምሰው ላይ ሊከሰት የሚችልና እንደማንኛውም ሕመም ሊረዳ (ሊታከም) የሚችል ነው**

ለምሳሌ፣ 'ስኪዞፌርኒያ' እና 'ባይ ፖላር' የተሰኙት የአእምሮ ሕመሞች በአብዛኛውን ጊዜ ከሠላሳ ዓመት በታች ባለ የእድሜ ክልል /ምርታማ መሆን በሚጀምርበት ጊዜ ላይ የሚከሰቱ በመሆናቸው በስራ እና በማሕበራዊ ሕይወት ላይ ትልቅ ተፅእኖ ያሳድራሉ::

ይህ የአዕምሮ ሕመም በአብዛኛው በወጣትነት የዕድሜ ክልል ላይ ከሚከሰትባቸው ምክንያቶች አንዱ ስነ-ህይወታዊ በሆነ መልኩ በጉርምስና ዕድሜ እንደሚካሄዱ አካላዊ ለውጦች በተመሳሳይ ሁኔታ በአዕምሮአችን ውስጥ ከሚከሰት ለውጥ የሚፈጠር ነው::

በጉርምስና እድሜ ክልል ውስጥ በአእምሯችን ላይ የሚካሄዱት የለውጥ ሂደቶች በትክክለኛው መንገድ ሲቀጥሉ ጤናማ የሆነ የወጣትነት ዕድሜ ይኖራል፤ በተወሰኑ ሂደቶች ላይ ደግሞ ዕክል ወይም ችግር ሲያጋጥም ተፅንኦ ይኖረዋል:: የአእምሮ ሕመም እንዲከሰት ምክንያት ሊሆን ይችላል::፣

ከዚህም ባሻገር ከሱስ ጋር ያሉ ችግሮች የሚጀምሩት በአብዛኞቹ በወጣትነት ዕድሜ ላይ መሆኑ እና በተጨማሪም ከወጣትነት ዕድሜ በኋላ ሰዎች ቤተሰብ ስለሚመሰረቱና ኃላፊነት ስለሚሰማቸው ብዙ ጊዜ ሰዎች የወጣትነት ዕድሜን ካለፉ በኋላ የተረጋጋ ሕይወት ይኖራቸዋል:: ይህ ደግሞ የአዕምሮ ሕመም በቀላሉ እንዳይፈጠር፣ ቢፈጠርም በአፋጣኝ እንዲታከሙ ያስችላል::

የአዕምሮ ሕመም በወቅቱ ሕክምና ካላገኘ ለማከም አስቸጋሪ ቢሆንም፤ ሕክምናውን በቅድሚያ መለየትና ማከም ከተቻለ የአዕምሮ ሕመም እንደማንኛውም ሕመም ታክሞ መዳን ይችላል::

ለምሳሌ፣ የህጻንትን የአእምሮ ሕመምን ብንመለከት፤ በማሕበረሰባችን ውስጥ የአዕምሮ ህመም ችግሮች የሚያጋጥማቸው አዋቂዎችን ብቻ እንጂ ሕፃናት በአዕምሮ ሕመም የማይጠቁ አድርጎ የመውሰድ የተሳሳተ ግንዛቤ አለ:: የአዕምሮ ሕመም ሁሉም ሰው ላይ ሊከሰት የሚችልና እንደ ማንኛውም ሕመም ሊረዳ (ሊታከም) የሚችል ነው::

የእእምሮ ሕመም በጉርምስና እድሜ ክልል ውስጥ ብቻ ሳይሆን በሕፃናት ላይም ሊከሰት ይችላል:: ነገር ግን በሕጻናት ላይ የምናያቸው የአዕምሮ ሕመሞች በሌሎች እድሜ ክልሎች ላይ ከሚታዩት ሊለይ ይችላል:: አንዳንድ ጊዜም እንደ እድሜያቸው ክልል የተለያዩ ዓይነት ችግሮችን በብዛት ልናስተውል እንችላለን::

ለምሳሌ፣ ከእድገት ጋር ተያይዞ የሚመጡ ችግሮች (Neuro Developmental Disorder) የሚጠቀሱ ናቸው፤ እነዚህም የአዕምሮ እድገት ውስንነት (Autism)፣ መንቀዥቀዥ፣ ንግግር ወይም መግባባት ላይ የመዘግየት ሁኔታ በልጆች ላይ በብዛት ልናስተውል የምንችላቸው ናቸው። ከጭንቀትና ከፍርሃት ጋር የተያያዙ ችግሮችም ሌሎች ናቸው::

በዋናነት በአዋቂ ሰዎች ላይ በብዛት ጎልተው የሚታዩ፤ የባህሪ ችግር የአዕምሮ ህመም አይነቶች በህጻናትም ላይ ጎልተው ይታያሉ (Oppositional Defiant Disorder)፤ እነዚህም እምቢተኝነት፣ መጨቃጨቅ፣ አለመታዘዝ፣ ሃይለኛ መሆን፣ መስረቅ ወዘተ ናቸው::

ከዚህ በተጨማሪ ሌሎች አዋቂ ሰዎች ላይ የምናያቸው የአዕምሮ ህመሞች ልጆች ላይም ልናስተውል እንችላለን:: ለምሳሌ፣ የጭንቀት (Anxiety Disorder)፣ ድብርት (Depression)፣ ዕድሜያቸው ከፍ እያለ ሲመጣም (በጉርምስና ወቅት) የሁለት ተቃራኒ ጫፎች ተለዋዋጭ ስሜት (Bipolar Disorder)፣ ስኪዞፍሬኒያ (Schizophrenia) እና ለሱስ ተጋላጭ የሚሆኑበት ዕድሜ ስለሚሆን ከእርሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የአዕምሮ ሕመም ችግሮች ሊኖራቸው ይችላል::

ግማሽ የሚሆነው የአዕምሮ ሕመም የሚከሰተው ከ18 ዓመት በታች በሆነ የእድሜ ክልል ውስጥ በመሆኑ ችግሩ ቀላል የሚባል አይደለም:: እነዚህ የአእምሮ ሕመሞች በተለያዩ ምክንያቶች የሚከሰቱ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ በማሕበራዊ፤ በአካላዊ ጉዳትና በባዮሎጂካል ለውጦች ሊከሰቱ ይችላሉ:: እነዚህ የአእምሮ ሕመሞች ሲከሰቱም በአፋጣኝ ወደ ጤና ተቋማት መሄድና ተገቢውን እርዳታ ማግኘት ያስፈልጋል::

በዚህ መልኩ ችግሩ ሲከሰት ተገቢውን ክትትልና የሕክምና መፍትሄ እንዲያገኙ ማድረግ ከቻልን፤ ለበሽታው ያለን ተጋላጭነት መቀነስ ይቻላል:: ለምሳሌ፣ የአዕምሮ ሕመም መምጫዎቹ ብዙ ቢሆኑም ሕመሙን ለማከምና ስርጭቱን ለመቀነስ ማሕበራዊ መስተጋብሮች ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል::

ለአብነት፣ ባደጉት ሀገራት በየዓመቱ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ራሳቸውን ያጠፋሉ:: ለዚህም እንደምክንያትነት የሚጠቀሰው የብቸኝነት ስሜት መኖር ነው፤ ይህ የሆነውም በብዛት ግላዊነት የበዛበት ኑሮ ስላላቸው ነው:: ይህ ጉዳይ በኛ ማሕበረሰብ ዘንድ እንብዛም ያልተለመደ በመሆኑ ሰዎች የሀዘን ጊዜያቸውን ሆነ የደስታ ጊዜያቸውን የሚጋሯቸው ወዳጅ፤ ዘመድና ጎረቤቶች አሏቸው::

ይህም ለአእምሮ ጤናቸው ከፍተኛ አስተዋጾ የሚኖረው በመሆኑ፣ ይህንን ጉዳይ ማስቀጠል ያስፈልጋል:: ከዚሁ ጋር ተያይዞም ሰዎች በማሕበራዊ ሚዲያ ላይ የሚያጠፏቸውን ጊዜያት በመቀነስ ከቤተሰቦቻቸውና ከጓደኞቻቸው ጋር የሚኖራቸውን ጊዜ ማጠናከር ይገባቸዋል::

ቤተሰብ ልጆች ላይ የባህሪ ችግር የሚመስሉ ባህሪያትን እና ልጆቻቸው የእድሜ እኩዮቻቸው የሚያደርጓቸውን ነገሮች ማድረግ ካልቻሉ፤ ማለትም ንግግር መጀመር በሚገባቸው ሰዓት ካልጀመሩ፤ መንቀሳቀስ መጀመር ባለባቸው እድሜ እንቅስቃሴ ካላሳዩ ወደ ጤና ተቋማት በመውሰድ የሕክምና እርዳታ የሚያገኙባቸውን መንገድ ቢፈልጉ ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት ያስችላል::

በተጨማሪም መንግስት ያለውን የአእምሮ ሕመም ስርጭት ለመቀነስና ሰዎች በአፋጣኝ ሕክምና እንዲያገኙ ለማስቻል የአገልግሎቱን ሰጭ ተቋማት ማስፋትና በዘርፉ የተማሩ ባለሙያዎችን ቁጥር ለመጨመር መስራት ይገባዋል:: በዚህ መልኩ ሁሉም የየራሱን ድርሻ ወስዶ ከሰራ፣ የአእምሮ ሕመም ችግርን መቀነስና የሚፈጥረውን ሁለንተናዊ ጫና መከላከል ይቻላል::

# ስፖርት





## ተጠባቂው የአፍሪካ ቦክስ ኮንፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ዛሬ ይታወቃል

**ብርሃን ፈይሳ**

ኢትዮጵያ ስኬታማ ከሆነችበት የአትሌቲክስ ስፖርት ባሻገር በቦክስና በብስክሌት ስፖርቶች በተደጋጋሚ በኦሊምፒክ መድረክ ላይ መሳተፍ ችላለች። በእነዚህ ስፖርቶች ከተሳትፎ ባለፈ ውጤት ሊመዘገብ ግን አልቻለም። ሆኖም በስፖርቶቹ ላይ ትኩረት ተደርጎ ቢሰራ እምቅ አቅም ያላት መሆኑን ባለሙያዎች ይመሰክራሉ። በቅርቡ በአፍሪካ የቦክስ ቻምፒዮና ላይ ለ2024 የፓሪስ ኦሊምፒክ ማጣሪያ በ57 ኪሎ ግራም የብር ሜዳሊያ ያጠለቀው ቦክሰኛ ፍቅረማርያም ያደሳም ለዚህ ማሳያ ይሆናል።

በስፖርት ዘርፍ በአፍሪካና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ከመሆን ባለፈ ተቋማቱን በመምራትም ሃገርን መወከል ትልቅ ዋጋ ይሰጠዋል። ለዚህ ደግሞ «የአፍሪካ ስፖርት አባት» እስከመባል የደረሱትን ታላቁ የስፖርት ሰው ይድነቃቸው ተሰማን ማስታወስ ይቻላል። የስፖርት ተሳታፊነት እና ማሕበራትን በማቋቋም በአፍሪካ የጎላ ሚና ያላት ኢትዮጵያ ከዓመታት ወዲህ ግን አህጉር አቀፍ የስፖርት ማሕበራትን ከመምራት ጋር ያላት ዝምድና እምብዛም እየሆነ መጥተል። በጥቂቱ ሊጠቀሱ የሚችሉና በዞን እና በአፍሪካ የስፖርት ተቋማት ውስጥ የመምራት እድልን ያገኙ የስፖርት አመራሮችም ቢሆኑ እንቅስቃሴያቸው የተቀዛቀዘ ሊባል የሚችል ነው።

አህጉር አቀፍ የስፖርት ማሕበራት መሪነት ሚናን በተለያዩ ስፖርቶች ወደ ኢትዮጵያ ለማምጣት የተለያዩ ስራዎች እየተከናወኑ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ አንዱ የቦክስ ስፖርት ፌዴሬሽን ተጠቃሽ ነው። ይኸውም ዛሬ የሚከናወነውን የአፍሪካ ቦክስ ኮንፌዴሬሽን ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ተከትሎ ኢትዮጵያዊ ተፎካካሪ ማቅረብ ተችሏል። የአፍሪካን የቦክስ ስፖርት የሚመራው ኮንፌዴሬሽን በጠራው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ በቀድሞው ፕሬዚዳንት ምትክ ዛሬ ምርጫ ያካሂዳል። 50 አባል ሃገራት ያሉት ኮንፌዴሬሽኑ ምርጫውን ባለፈው ወር ለማድረግ ያቀደ ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቶች ተራዝሞ ነው ዛሬ የሚደረገው።

በደቡብ አፍሪካዋ ከተማ ደርባን በሚካሄደው በዚህ የፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ላይም አስፈላጊውን መስፈርት አሟልተው የተገኙ አራት እጩዎች መቅረባቸው ተረጋግጧል። እነሱም ከኢትዮጵያ አቶ እያሱ ወሰን፣ ካሜሮናዊው ሜንዶጋ ቤርትራንድ ሮናልድ፣ ሞሮኳዊው አል ካቡሪ ሞሃመድ እንዲሁም ከዚህ ቀደም በኮንፌዴሬሽኑ ምክትል ፕሬዚዳንት ሆነው ሲሰሩ የቆዩት ናይጄሪያዊው ኦሞ አጌጌ አዛኒያ ናቸው። ኢትዮጵያን በመወከል በምርጫው ላይ የሚሳተፉት የፓራዳይዝ ሎጅ እና የኦሞቲክ ቢዝነስ ግሩፕ ባለቤትና ባለሀብቱ አቶ እያሱ ከፍተኛውን ድምጽ በማግኘት የመመረጥ እድላቸው የሰፋ እንደሚሆን ተጠቁሟል።

አቶ ኢያሱ ለቦክስ ስፖርት ካላቸው ፍቅር የተነሳ ስፖርቱን በእውቀታቸው እንዲሁም በገንዘባቸው ለማገዝ እንደተቀላቀሉ ይታወቃል። ይህንንም በሚካሄዱ ውድድሮች ላይ ተገኝተው ለአሸናፊዎች በሚያደርጉት የገንዘብ ሽልማትና ድጋፍ በተደጋጋሚ ማስመስከር ችለዋል። አሁን ደግሞ በዚህ ስፖርት የአፍሪካ ፕሬዚዳንት በመሆን የሃገራቸውን ስም ለማስጠራት በእጩነት ቀርበዋል። የመወዳደሪያ መሪ ሃሳባቸው «ነፃ አፍሪካ አንድ የቦክስ ራዕይ» ሲሆን፤ ነጻ አህጉር የሆነችው አፍሪካ ነጻ መሪ ያስፈልጋታል የሚል መርህ እንደሚከተሉም አስተዋውቀዋል።

እጩው አቶ ኢያሱ የኮንፌዴሬሽኑ ፕሬዚዳንት በመሆን ቢመረጡ ለኢትዮጵያ የቦክስ ልማት ከሚኖረው ጠቀሜታ ባለፈ በስፖርት ዲፕሎማሲ ረገድ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ እንደሚሆን ይጠቁማሉ። በተጨማሪም በገጽታ ግንባታ፣ በገንዘብ፣ የስፖርት ማዕከላትን በማስገንባት እንዲሁም ዓለም አቀፍ እንዲሁም አህጉር አቀፍ ውድድሮች ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ የሚሰሩ መሆናቸውንም የምርጫ እንቅስቃሴ ባደረጉበት ወቅት ጠቁመዋል። አክለውም «ምርጫው አህጉር አቀፍ ስፖርትን ለመምራት የሚደረግ በመሆኑ ለኢትዮጵያ የቦክስ ስፖርት መልካም ዕድል የሚፈጥር መሆኑን አብራርተዋል። የኮንፌዴሬሽኑ አባላት ለአፍሪካ የቦክስ ስፖርት ትክክለኛና የሚበጀውን ሰው መምረጥ አለባቸው» ሲሉም ተናግረዋል።

የምርጫ እንቅስቃሴያቸውን ተከትሎም የታንዛኒያ እና ሶማሊያ ቦክስ ፌዴሬሽኖች ድጋፋቸውን ያሳዩ ሲሆን፤ አቶ ኢያሱ በንግዱ ዓለም ያገኙትን ስኬት በኮንፌዴሬሽኑም መቀዳጀት እንደሚችሉ እንዲሁም ስፖርቱንም ያሳድጋሉ የሚል እምነት እንዳላቸው ገልጸዋል።



አቶ ኢያሱ ወሰን የአፍሪካ ቦክስ ኮንፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት የመሆን እድል አላቸው፣


## የግልፅ ጨረታ ማስታወቂያ
## ፈ/ህ/አጠ/ስፔ/ሆ 0005/16

የፈለገ ህይወት አጠቃላይ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በ2016 በጀት ዓመት አጠቃላይ በሆስፒታል ግቢ ውስጥ የገፀ ምድር ማስዋብ ወይም አትክልትና አካባቢ /ግሪን ኤሪያ/ እንክብካቤ ስር አውትሪሶርስ አድርጎ ለአንድ ዓመት ውል በመውሰድ ለማሰራት፣ የተለያዩ ሪኤጀንትና ስፐላይስ ግዥ እና የተለያዩ የህትመት ስራዎችን፣ የህንፃ መሳሪያ የጥፃና እቃዎች ማንኛውንም ወጭን ጨምሮ አጠቃላይ ግብርና ታክሱን ሸፈኖ በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛትና ለማሰራት ይፈ ልጋል፡፡ በመሆኑም

**በዚህ ጨረታ የሚወዳደሩ ድርጅቶች፡ -**

1. በዘመኑ የታደሰና በዘርፉ ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ያላቸው እና የግቢ አትክልትና አካባቢ/ግሪን ኤሪያ/ እንክብካቤ የአንድ ዓመት እና ከዚያ በላይ ስራ ልምድ ከመንግስታዊ መ/ቤት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ
2. የግብር ከፋይነት መለያ /TIN CARD/ ሰርቴፊኬት ያላቸው፣
3. አጠቃላይ የገንዘቡ መጠን ከብር 200,000.00/ሁለት መቶ ሽህ ብር /እና በላይ ከሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ /VAT/ ከፋይነት የተመዘገቡ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ፡፡
4. ተጫራቾች በጨረታ ለመሳተፍ ከላይ ከተቁ 1-3 የተጠቀሱትን የሚመለከታቸውን ማስረጃዎች ፎቶ ኮፒ ከመጫረቻ ሰነዶቻቸው ጋር አያይዘው ማቅረብ አለባቸው፡፡
5. አጠቃላይ ስለ ጨረታው ዝርዝር መግለጫ /እስፔስፊኬሽን/ እና የጨረታ መመሪያ ከጨረታ ሰነዱ ጋር ተያይዟል፡፡
6. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን የማይመለስ ብር 200.00 /ሁለት መቶ ብር/ ብቻ በመክፈል ከሆስፒታሉ ዋና ገ/ያዥ ቢሮ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት በተከታታይ 16 ቀናት ዘወትር በስራ ሰዓት መግዛት /ማግኘት/ ይችላሉ፡፡
7. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና /ቢድ ቦንድ/ለሚወዳደሩብ የገፀ ምድር ማስዋብ ወይም አትክልትና አካባቢ/ግሪን ኤሪያ/ እንክብካቤ _ አገልግሎት ስራ ጠቅላላ የአንድ አመት ዋጋ የሚሞሉትን ማንኛውንም ግብር እና ታክስ ጨምሮ 20,000.00/ሃያ ሽህ ብር/ እና የተለያዩ ሪኤጀንትና ስፐላይስ ግዥ እና የተለያዩ የህትመት ስራዎችን የህንፃ መሳሪያ፤ የጥገና እቃዎች 2% በባንክ በተረጋገጠ የክፍያ ትዕዛዝ /ሲፒኦ! ! በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና / ቢድ ቦንድ ወይም በሆስፒታሉ የጥሬ ገንዘብ ደረሰኝ ገቢ በማድረግ ዋናውን ደረሰኝ ከፖስታው ውስጥ አብረው ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡
8. ማንኛውም ተጫራች የጨረታ ሀሳቡን በአማርኛ ቋንቋ ስርዝ ድልዝ ሳይኖር በዋጋ ማቅረቢያው ቅፅ መሰረት የአንዱን ወር ዋጋና የ12 ወራት ጠቅላላ ድምር ዋጋ በመመላት የድርጅቱን ህጋዊ ማህተም፣ፊርማና አድራሻ በማስቀመጥ በጥንቃቄ በታሸገ ፖስታ በሆስፒታሉ የግዥ ኦፊሰሮች ቢሮ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ዘወትር በሥራ ሰዓት ይህ ጨረታ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ ባሉት ተከታታይ 16 ቀናት 4:00 ሰዓት ድረስ ማስገባት ይኖርባቸዋል ሳጥኑም በዚሁ ዕለት ከቀኑ 4፡15 ይታሸጋል፡፡
9. ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በሆስፒታሉ ቢሮ በዚሁ ቀን ከቀኑ በ4፡ 30 ሰዓት ይከፈታል፡፡ ቀኑ በዓል /ዝግ /ከሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን ከላይ በተጠቀሰው ተመሳሳይ ሰዓት ይከፈታል፡፡
10. ሆስፒታሉ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን መሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡
11. በጨረታው የሚሳተፉ አካላት ስለጨረታው ዝርዝር መረጃ ማብራሪያ/ከፈለጉ በአካል በመምጣት ወይም በስልክ ቁጥር 0583205738/058 222 0916 በመደወል ማግኘት ይችላሉ፡፡

**አድራሻ፡-**

**ፈለገ ህይወት አጠቃላይ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል**

ባህርዳር

**የፈለገ ህይወት አጠቃላይ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል**



## ጉዳዩ- የግልፅ ጨረታ ማስታወቂያ
## ጨረታ ቁጥር 02/2016 ዓ.ም

በቂርቆስ ክ/ከተማ የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት የመንግስት ግዥ ቡድን ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ላይ ተጫራቾችን በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ዕቃ መይም አገልግሎቱን መግዛት ወይም ማግኛት ይፈልጋል፡፡

የጨረታ ማስከበሪያ

ሎት.1 ዘመናዊ የሙዚቃ መስሪያ 50000

ሎት.2 የባህል አልባሳት 15000

ሎት.3.የካፍቴሪያ አግለግሎት 30000

ሎት4. አላቂ የፅዳት ዕቃዎች 2000

ሎት5 አለቂ የቢሮና የፅፈት መሳራዎች 6000

በዚህም መሰረት ከዚህ በታች የተጠቀሱትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች በጨረታ እንዲሳተፉ እንጋብዛለን፡፡

1.የዘመኑን ግብር የከፈሉ በዘርፉ ህጋዊ የታደሰ የንግድ ስራ ፈቃድ እና የንግድ ምዝገባ ሰርቲፍኬት በአቅራቢነት የተመዘገቡ የግብር ከፈያ መለያ ቁጥር/TIN NO/ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሰርተፍኬት ያላቸው፡፡

2.የጨረታ ስነድ አቀራረብ ቴክኒካል ሰነድ ኦርጅናል፣ቴክኒካል ሰነድ ኮፒ፣ፋይናንሻል ሰነድ ኦርጅናል፣ፋይናንሻል ሰነድ ኮፒ ለየብቻው እንዲሁም ሲፒኦ /CPO/ በባንክ የተረጋገጠ ለብቻ በታሸገ ኢንቨሎፕ ማቅረብ አለበት፡፡

3.በጨረታው ላይ ጥቃቅን አነስተኛ ይበረታታሉ ሆኖም ግን የጨረታ ሰዱን በነጻ ለማግኘት የሚችሉት ከተቋማት የበላይ ኃላፊዎች ተገቢና የተሞላ ማስረጃ ሲያቀርቡ ብቻ ነው፡፡

ወቅታዊ የሆነ የመልካም አፈጻጸም የስራ ልምድ ሲያቀርቡ ብቻ ነው፡፡

5.ተጫራቾች የሚያቀርቡትን ናሙናዎች ጨረታው ከመከፈቱ ከሁለት ቀን በፊት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

6. በሎት 3 ላይ የተጠቀሰ የካፍቴሪያ አግልግሎት የራሱ ቆጣሪ አሰተዳደሩ ስለማያስገባ የሙብራት ክፍያ አሸናፊው የሚከፍል ይሆናል፡፡ እንዲሁም በአስተዳደሩ የሚሰጡ ማንኛውም መስተንግዶ፣የስልጠና ናየምግብ አገልግሎቶች ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡ በተጨማሪ የምግብ ዝርዝር የሚቀርብበት ሰዓት ለሰራተኛው አስፈላጊ የሆነ ምግብ ዝርዝሮች ትኩረት ማድረግ አለበት

7.ተጫራቾች የሚጨረቱበትን ዋጋ በገዙበት ሰነድ ላይ ባለው የዋጋ ማቅረቢያ ቫትን ጨምሮ ማስገባት ይኖርበታል፡፡

8. የጨረታ ሰነዱን እስጥፋኖስ ቤ/ክርስቲን አከባቢ በሚገኘው የቂርቆስ ክ/ከተማ አስተዳደር ህንጻ 6 ኛ ፎቅ የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት ይፋናንስና አስተዳደር የግዥ ቡድን በማቅረብ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ 10 ታከታታይ የስራ ቀናት የሚቆይ ሲሆን የሚከፈተው ደግሞ በ11 ኛው ቀን ላይ ከጠዋት 4፡00 ሰዓት ተጫራቾች በተገኙበት የጨረታ ሳጥኑ የሚዘጋ ሲሆን በተመሳሳይ ቀን ከጠዋቱ 4፡30 ላይ ጨረታው ይከፈታል፡፡

9. አሸናፊ ድርጅት አሸናፊነቱ ከተገለጸለት ለ7 ተከታታይ የስራ ቀናት በኃላ በግንባር ቀርቦ አሸናፊ የሆነበትን ጠቅላላ ዋጋ 10 በሙቶ የውል ማስከበሪያ በማስያዝ 8 የስራ ቀናት ውስጥ ውል መያዝ አለበት፡፡

10 መስሪያ ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በክፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው ፡፡

አዳራሻ፣ እስጢፋኖስ ከሚገኘው ከማሪዎት ሆቴል ፊትለፊት የቂርቆስ ክ/ከተማ አስተዳደር 6ኛ ፎቅ ስልክ ቁጥር 0115582871

**በቂርቆስ ክ/ከተማ የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ጽ/ቤት**